ኢየሱስ በልጅነቱ

የማቴዎስ 2 ና ሉቃስ 2:21-52 ሪክ

ኪቲ አና ግሪፊትስ

ሥዕል በ«ዊሊ»

ትርጉም፡- ይሌ ጀናይ

ርማት፡- ዮዲት ይሉ ና ዳንኤል ተሾመ

ዋና አር ዒ፡- ዘነበ ገብረሐና

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING

መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረጉ መጻሕፍት
የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ ክፍል

የአሳ ሚው መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright
© 2006 by SIM Ethiopia, Addis Ababa.
Originally published in English under the title of
JESUS the Boy. Copyright © Kithy Anna Griffiths 1976.
Colour edition 2002. Bible Stories Alive.
A division of A visit with Mrs. G. Minitries Inc.
2851 St. Clair Avenue East, Toronto, Ontario, Canada M4B 1N4

የመጀመሪያ ትም 2001 ዓ.ም (2009)

አሳ ሚ፡- የኤስ ኣይ ኤም ሥነ ጽሑፍ
የፖ.ሣ. ቁጥር 127፣ አዲስ አበባ
ስልክ 011-551-2973፣ 011-349-3252
ኢ..ሜይል፡- simmedia @ethionet.et

የኮምፒውተር ጽሑፍ፡- ጥሩ ወርቅ በቀለ
የገጽ አቀማመጥ፡- ዓለም ፀሐይ ውነቱ

በኤስ ኣይ ኤም ማተሚያ ቤት ተመ።

ሪኮች

1. አንድ ደማቅ አዲስ ኮከብ 5
2. ንጉሥ ሄሮድስ ተቈጣ 14
3. ስሙም ኢየሱስ ይባላል 21
4. «ኑና መሚሑን ዩት!» 28
5. «አይተነዋል!» 34
6. «ወንድ ሕፃናት ሁሉ ይገደሉ!» 45
7. አናጢ ለመሆን መሠልጠን 56
8. የአባቱ ሥራ 67

ስ ውሳላችሁን? 78

ኢየሱስ በልጅነቱ ስራኤል



1

አንድ ደማቅ አዲስ ኮከብ

ግዚአብሔርን ገና የማያውቁ ኮከብ ቈጣሪዎች («ሰብአ ሰገል»)፣ ለመጭው ሳምንት ፋርስ ውስጥ ለሚ ተም ጋዜጣ «በኮ ከብ ቈጠራ ዓምድ» ላይ የሚወጣ ጽሑፍ ይጽፉ ነበር። ይህንን ሥራ ለዓመ ት ያህል ሠርተው ል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ በሚጽፏቸው ነገሮች አማካይነት በሺዎች የሚቈጠሩ ሰዎችን ሕይወት መርተዋል። ነዚህ ኮከብ ቈጣሪዎች ሞኞች አልነበሩም። ስለ ብዙ ነገሮች ብዙ ውቀት ነበራቸው - ስለ ሳይንስ፣ ፍልስፍና፣ ስለ ሃይማኖት ጕዳዮች - ንዲሁም ሰዎችን ንዴት ንደሚስቡ ያውቁ ነበር።

ሰዎች ኮከብ ቈጣሪዎችን በአክብሮትና በፍርሃት ከፍ አድርገው ያይዋቸው ነበር። የወደ ፊቱን የሚያነብቡና ያለፈውን የሚመ ረምሩ ጠንቋዮች አድርገው ይቈጥሯቸው ነበር። ነዚህ «አስማተ ኞች» ከትልቅ ቤተሰብ የተወለዱ ባላባቶች ነበሩ። ጅግ ባለጠጎች ስለ ነበሩ ለመኖር መሥራት ንኳ አያስፈለጋቸውም ነበር። ስለዚህም ጊዜያቸውን በሙሉ የሚያጠፉት በመማር ነበር።

መቼ መትከል፣ መቼ መሥራትና መቼ ማጨድ



ንደሚገባቸው ለሰዎች ይነግሩ ነበር። ትኩረ ቸውን ሁሉ በ ነዚህ ኮከብ ቁጣሪዎች ላይ ያደረጉ ሁሉ፣ በኮከብ ቁጠራ ምክንት ባርነት ውስጥ ነበሩ፤ ብዙዎችም በዚሁ ምክንት ውስጥ ገብተው ነበር። (በአሁን ጊዜም በአንዳንድ ጋዜጦች ላይ ጀሚኒ፣ ሊብራ፣ ካፕሪኮርን፣ ወዘተ. . . የሚሉ ቃላት ትሰማላችሁ።)

የኮከብ ቁጣሪዎች መሪ የሆነው ጋስጳር፣ ተናገረ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጋስጳር ሁኔ ው ሁሉ ልክ አልነበረም፣ ጥርጣሬ የገባው ይመስል ነበር። ሥራውን ለመሥራት ከተፈለገ በዚህ ጉዳይ ላይ ጥርጣሬ የሚባል ነገር መኖር አልነበረበትም።

ጋስጳር ጮክ ብሎ ንዲህ አለ፦ « ነሆ፣ ኛ በትንቢ ችን አማካይነት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት ንቄጣጠራለን ወይም ንገዛለን።» ቀጥሎም በማንባረቅ፣ «ፈጣሪ የሆነና የፈጠራቸውንም ሰዎች የሚወድድ አንድ ላቅና መልካም አምላክ ንዳለ አምናለሁ። ሰዎች በ ርሱ ላይ ከተማመኑ፣ የሚያስፈራቸው ምንም ነገር አይኖርም። ክቡራን ወገኖቼ፣ ይቅር አድርጉልኝ። ለ ኔ የሚሰማኝ ንዲህ ነው።»

ጋስጳር በዚያን ሌሊት መተኛት አልቻለም። ውጭ ወጥቶ ከ ላቁ ሰማይ ጣራ ሥር ያሰበ ይንጐራደድ ነበር። ጆቹን ወደ ኋላው አድርጎ፣ ዓይኖቹን በሚራመድበት በጨለማ መንገድ ላይ አፍጥጧል። በድንገትም፣ በደማቅ ሰማያዊ ብርሃን አማካይነት መንገዱን በግልጥ ሊያየው ቻለ። በዚህ ጊዜ ጋስጳር ወደ ላይ ቀና አለ። በሰማዩም ላይ አዲስ ደማቅ ብርሃን አየ።

አሁን፣ በፊት ለፊቱ ያለውን ሰማይ ንደ ጁ ጀርባ አወቀው - ያንዳንዱ ኮከብ በነጠላ፣ ንዲሁም በ ብረት ሆነው በግልጥ ዩት። ይህ አዲስ ብርሃን የአንድን ነገር አመልካች ነበር። ከዚያ ጊዜ በፊት አልነበረም። በፍጹም፣ አልነበረም! ጋስጳር በምሥራቃዊው ሰማይ ክፍል በኩል ተንጠልጥሎ አየው። ቀስ ያለ ወደ ላይ ከፍ ያለ ወጣ። ለደቂቃዎች ያህል፣ ጋስጳር በድን ሆኖ ቀረ። ከዚያ በኋላ ጮክ ብሎ፣ «ይህ አዲስ ነገር ነው። ይህ

ልዩ ነገር ነው። ይህ ስፈልገው የነበረው ከአምላክ የተላከ መልእክት ነው። ለሌሎቹም መንገር አለብኝ፣» አለ።

በጣም የመሸ ቢሆንም፣ ጋስጳር ወደ ሥራ ጓደኞቹ መኖሪያዎች ሄዶ፣ «ስለ ቀሰቀስኳችሁ ይቅር ፣» አለና በመቀጠል፣ «መቀስቀሴ ግን ጠቀሜ ንዳለው ትገነዘባላችሁ። ኑ! ተመልከቱ!» አላቸው።



ወዲያውኑ ኮኮብ ቄጣሪዎቹ ሁሉ መጨረሻ ላይ በተቀሰቀሰው ሰው ቤት ደጃፍ ላይ ቆሙ። ዛው ዝም ብለው ቆመው ሰማይ ላይ በተንጠለጠለው በዚያ ደማቅ፣ ሰማያዊና አስደናቂ ክስተት ላይ አፈጠጡ።

« ንደ፣» አለ አንዱ በመጨረሻ፤ «ሁለት ወይም ሦስት ትላልቅ ከዋክብት አንድ ላይ ተገናኝተው መሆን አለበት። ቢያንስ ቢያንስ፣ አቅጣጫቸው ተገጣጥሞ ንደ አንድ ግዙፍ ኮከብ ሆነው ይተው ይሆናል።»

« ንደዚያ ከሆነ፣» አለ ሌላው፣ «ቶሎ ተለያይተው በየመንገዳቸው ይሄዳሉ። ነገ ማ ምን መሆኑን መናገር ንችላለን» አለ።

«ይህ ኔ የምፈልገው፣ ከ ግዚአብሔር የመጣ መልእክት

ንደ ሆነ አምናለሁ።» አለ ጋስጳር። በመቀጠልም፣ «ዛሬ ማ በሻማ መብራት ንኳ ቢሆን መጻሕፍቱን መረምራቸዋለሁ፤ ከ ናንተ መካከል የሚፈልግ ካለ፣ ከ ኔ ጋር መመርመር ይችላል።»

« ኔ መተኛት ይሻለኛል!» አሉ ብዙዎቹ በአንድ ላይ። «ነገ፣ ኮ ከቡ ዛው ካለ፣ መጻሕፍቱን ንመረምራለን።» አለ ከጥቂቶቹ መሀል አንዱ።

መልቂዮር ግን፡- «ጋስጳር፣ ኔ ከአንተ ጋር አነብባለሁ» አለ። ሮማውያን፡- «ለማኝ ሲሞት ባለ ጅራት ኮከብ አይ ይም፤ ልዑላን ሲሞቱ ግን ሰማያት ራሳቸው ይናገራሉ» የሚል ተረት አላቸው። ይህ ኮከብ ሞትን የሚያመለክት አይደለም። በጣም ደማቅ ነው። የሚያመለክተው መወለዱን ነው። ለማንኛውም መጻሕፍቱን አንድ ላይ ሆነን ንመረምራለን።»

« ኔም ከ ናተ ጋር ሆኜ መረምራለሁ» አለ ቤልጣሳር።



ከሌሎቹ መሀል ሁለቱ አቅማሙና ለመተኛት ወሰኑ። « ኛ ነገ ንመራመራለን። ያገኛችሁት ነገር ካለ ግን ንገሩን፣» ብለው ተኙ።

ነዚያ ሦስት ኮከብ ቈጣሪዎች በሻማ መብራት ተጠቅመው ሌሊቱን ሁሉ ብራናዎችን ሲያገላብጡ አደሩ። ተራ በተራ ወደ ውጭ የወጡ የኮከቡን ንቅስቃሴ ለመከ ተል ይሞክሩ ነበር። ኮከቡ ግን ከቦ ው አልተንቀሳቀሰም ነበር!

ጧት ሲነጋጋና ኮኮቡ ደግሞ ሲጠልቅ፣ ኮከብ ቈጣሪዎች ዘንድ አዲስ ብርሃን መጣ። አገራቸውን በተመለከተ ጽሑፋቸው ውስጥ ያገኙት ምንም ነገር አልነበረም። ስለ አይሁድ በሚናገሩ መጻሕፍት ውስጥ ግን በአሁኑ ጊዜ አንድ ንጉሥ በ ስራኤል ይወለድ ዘንድ ንደሚጠበቅ ማግኘት ችለዋል።

ጧት ከ ንቅልፍ ማጣትና ከድካም የተነሣ ዓይኖቻቸው ቢቀሉም፣ የሥራ ባልደረቦቻቸውን አንድ ላይ ጠርተው የትንቢቶቹን ቃላት አሳዩዋቸው።

« ንግዲህ ሄደን ርሱን ማግኘት አለብን፣» አሉ።



«የሚሄደው ማን ነው?»

«ምርምሩን ያካሄዳችሁት ናንተ ሦስ ችሁ ሂዱ፣» ተባብለው በዚህ ተስማሙ።

«ሕፃን፣ የአይሁድ ንጉሥ፣ ድንቅ ነው፤ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘ ው ቤተ መንግሥት ንሄዳለን። ምናልባት ንጉሥ ሄሮድስ ሞቶ ይሆናል። ሽምግሏል፤ በጣምም ምሞአል። አሁን ደግሞ አ ምሮው መ ወኩን ሰምቻለሁ። ብዙ ጊዜ አግብቷል - ምናልባትም አሥሬ ይሆናል። ብዙ ልጆችም ወልዷል። አብዛኞቹን ግን ስከ ናቶቻቸው ጭምር ገድሏቸዋል። ይህ አሁን የተወለደው ልጅ ግን ወራሹ መሆን አለበት።»

«ቶሎ ብለን መሄድ አለብን፣» አለ መልቂዮር።

«ስጦ ዎች!» አለ ጋስጳር በመደነቅ።

ቤልጣሳርም፣ « ንዴ፣ ስጦ ዎችስ?» አለ በጭንቀት።

«አዎን፣ ከሕፃኑ ንግሥና ጋር የሚመጥኑ ስጦ ዎችን ይዘን መሄድ ይኖርብናል። ወርቅ! አዎ፣ ወርቅ ለንጉሡ፣ ለሕፃኑ ንጉሥ። ልዩ ልዩ የወርቅ ዕቃዎች፣» አለ ጋስጳር።

«የአይሁድ ንጉሥ ካህንም ጭምር ንደሚሆን ትናንት ማ ከብራናው ውስጥ አንብቤያለሁ። አንድ ዘመን አንድ የ ወቀ ካህን ነበረ- ማን ነበር ስሙ? መል- መልከ- መልከ ጼዴቅ። አዎ፣ ትክክል ነው፣ ንጉሥ ና ካህን። ንጉሥ- ካህን ለሆነው ሕፃን ጥቂት ዕጣንም ይዘንለት መሄድ ይኖርብናል፣» ብሎ ወሰነ ቤ ልጣሳር።

« ንዴ ! ዕጣን በጣም ውድ ቢሆንም፣ ለሕፃኑ ንጉሥ የሚመጥን ስጦ ነው። ግን አለን ንዴ?» ሲል ጠየቀ ጋስጳር።

መልቂዮር ለአንዱ አገልጋይ፣ «ሂድና ይ!» አለው። «ምንም ንኳ ለአምልኳችን ብዙ ብንጠቀምም፣ በቂ ያለን ይመስለኛል። በጣም ጥሩ መዓዛ አለው። ውብ የሆነ መዓዛ።» አገልጋዩም፣ «አዎ፣ ብዙ አለ፣ ጌ ዬ» የሚል መልስ ይዞ መጣ።

«መልካም፣ ስጦ የሚሆን አንድ ጥቅል አዘጋጅልኝ፣» አለው መልቂዮር።

«ትናንትና ማ ብራና ላይ፣» አለ ቤልጣሳር፣ «የአይሁድ ካህንና ንጉሥ በሕይወቱ አንድ ቦ ላይ ንደሚሠቃይ አንብቤአለሁ፣ ስለ ከዋክብቱ ያነበብኩትን ግን አልነግራችሁም።»

ጋስጳርም፣ «ይህንን ሁኔ በተመለከተ ከብራናው በም ገኙት ላይ ብቻ አተኩሩ፣» አለ።


«'መሠቃየት'?» ብሎ መልቂዮር ጠየቀ። «ሁሉም ሰው በአንድ ወቅት ንደሚሞት የ ወቀ ነው። ይህን የሚያመለክተው ደግሞ ከርቤ ነው። አዎን፣ ከርቤ። ከስጦ ችን ጋር ከርቤም መ ከል አለበት። ከርቤ፣ ለመሆኑ ከርቤ ይኖረን ይሆን?» አለ መልቂዮር።

«አዎ፣ ጌ ዬ ብዙ አለ፣» ብሎ መለሰ አገልጋዩ።

« ንግዲህ ለስጦ አንድ ጥቅል ከርቤ አዘጋጅልኝ?። ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ፣ ነዚህ ይዘጋጁ» ሲል አዘዘ ጋስጳር። « ነዚህ ለሕፃኑ የምናቀርብለት ስጦ ዎች ይሆናሉ።»

«አሁን ለጕዟችን መዘጋጀት አለብን፣» አለ ጋስጳር። ብዙ ቀን






ሳይወስድብን አይቀርም። ብቃት ያላቸው አገልጋዮች፤ ግመሎችን የሚነዱ፣ ምግብ አብሳዮች፣ አልባሾች፣ ድንኳን ተካዮችና የጓዝ ጎላፊዎች ያስፈልጉናል» በማለት ዘረዘረ ጋስጳር።

ኮከብ ቄጣሪዎቹ በዚህ አጭር ጊዜ ባደረጉት ዝግጅት ውስጥ ሕፃኑን ንጉሥ ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎትና ጉጉት አደረባቸው።

ጋስጳር ሊ ገሥ አልቻለም። «በአንድ ትልቅ ግኝት ጅምር ውስጥ የገባሁ ይመስለኛል፣» አለ ራሱን በራሱ። « ውነተኛውን አምላክ ላገኘው ነው። አስቀድሞም፣ ራሱን የገለጠልኝ ንደ ሆነ ይሰማኛል። ኮከቡን ሌሊት ሌሊት አየዋለሁ። ርሱም ጠቀስ ያደ ረገ ወደዛ ማደ፣ ወደ ምድረ በዳ ንድመጣ ይጠራኛል። ይጠቅሰኛል፣ አሁንም ይጠቅሰኛል . . . »

ጠቢባኑ ኮከብ ቄጣሪዎች፣ አገልጋዮች፣ ግመሎች፣ ስንቅና ገጸ በረከቶቹ ሁሉ ዝግጁ ሆኑ።



«በዚህ ሌሊት፣ ደማቁ ኮከብ ሲወጣ ጉዟችንን ንጀምራለን፣» አላቸው ጋስጳር።

በርግጥም ጉዟቸውን ጀመሩ። በጉዟቸው ኮከቡ መራቸው። ጧት ጧት ኮከቡ ሲጠልቅ፣ ድንኳኖቻቸውን ይተክሉና ይተኙ ነበር። ማ ማ ኮከቡ ሲወጣ ደግሞ ተነሥተው ይከተሉት ነበር፣ ንደገና ጧት ሆኖ ኮከቡ ሲጠልቅ ይተኙ ነበር። ንዲህ ያሉ ቀጠሉ . . .»

«ነገ ኢየሩሳሌም ንደርሳለን፣» አለ ጋስጳር። «ነገ ወደ ቤተ መንግሥቱ ንገባና ለሕፃኑ ንጉሥ ጅ ንነግለን። ዛሬ ከከተማዋ ቅጥር ውጭ ንሰፍራለን። ነገ ጧት ወደ ላቁ ቤተ መቅደስ ሄደን በአሕዛብ አደባባይ (ግቢ) ውስጥ ንሰግዳለን፣ ከዚህ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥቱ ንገባለን፣» አለ።

2

ንጉሥ ሄሮድስ ተቈጣ

በማግሥቱ ከምሥራቅ የመጡቱ ሰብአ ሰገል ልብሳቸውን በጥንቃቄ ለበሱ። ለነበሩበት የኑሮ ደረጃ ብቁ አድርገው ክብር የሚሰጧቸውን ውብ ካባዎቻቸውን ደረቡ። ዛሬ ኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መንግሥት ውስጥ ገብተው ሕፃኑን የአይሁድ ንጉሥ ያዩ ል። ምናልባት ሄሮድስ ሞቶ ሊሆን ይችላል፣ ላይሞትም ደግሞ ይችላል። ነገር ግን፣ በቅድሚያ በ ላቁና ውብ በሆነው ቤተ መቅደስ መስገድ ነበረባቸው።

በዚያን ጧት በቤተ መቅደሱ የነበሩ የአይሁድ ዜጎች ሽክ ብለው ለብሰው በአሕዛብ አደባባይ የሚሰግዱትን ንግዶች ከማየት በቀር ምንም ማድረግ አልቻሉም።

«ምናልባት በጉዟቸው በደ ና ስላደረሳቸው አምላካችንን ያመሰግኑት ይሆናል፣» ብላ አንዷ ሴት ለሌላዋ ነገረቻት።

ከስግደቱ በኋላ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሄዱ።

አንድ አስተናጋጅ በሩን ከፈተላቸው።



«የመጣነው ለሕፃኑ ጅ ለመንሣት ነው፣» አለ ጋስጳር።

«ሕፃኑን?» አለ ግራ የተገባው አገልጋይ በትሕትና። መቼም ነዚህ ሽክ ያሉ ጠጉረ ልውጥ ሰዎች ሞኞች ሊሆኑ አይችሉም። «ጌቶቼ፣ ሕፃኑን ነው ያላችሁት? ዚህ ሕፃን የለም። በስሕተት መሆን አለበት።»

«ሕፃኑን ንጉሥ ኮ ነው የፈለግነው። የአይሁድ ንጉሥ ማለ ችን ነው። ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ተከትለነው መጣን። ልናየው የግድ ነውና፣ ባክህን። ዚህ አካባቢ ንዳለ ናውቃለን።»

ሌሎች የቤተ መንግሥቱ አገልጋዮች ሥራቸውን ለማከናወን ሲንቀሳቀሱ ለየት ያሉትን ንግዶቹን አዩዋቸው። ብዙ ግርግር ነበ ረ።

«ጌቶቼ፤ ያለን ንጉሥ፣ ሄሮድስ ብቻ ነው። ርሱ ደግሞ ሽም- ግሎሏል፣ ምሚልም። ንዳይረበሽ ቀስ ብላችሁ ተናገሩ፣ አትጩኹ» አላቸው አስተናጋጁ።

ንዳይጮኹ ያስጠነቀቃቸው በጣም ዘግይቶ ነበር። የሄሮድስ ተ ጠራጣሪ ጆሮዎች ከምን ጊዜውም በላይ ክፍት ነበሩና የተባለውን ሁሉ ቀሰቡት። «ሕፃኑ ንጉሥ . . . የአይሁድ ንጉሥ፣» የሚሉት ቃላት ነበሩ ለዛ ባለው ድምፀት የተነገሩት። አልጋው ላይ ሆኖ ንደ ብድ አስለፈለፈው። ነዛ ደም የለበሱ ዓይኖቹ በድንጋጤ ፈጠጡ። ያ ቀጡ አፉ ተከፍቶ ቀረ፣ ጆቹም ንደ ንቍራሪት መዳፍ ደርቀው ቀሩ፣ ትራሱን ጭብጥ አደረገው።

ንጉሥነቱን ለማሳየት ሞከረ።

«ወደዚህ፣ ወደ ኔ አምጣቸው!» ብሎ ጠባቂውን አዘዘው።



«ግን ፡ኮ - ነገር ግን ግርማዊነትዎ፣ ርስዎ፣ - ርስዎ ፡ኮ ንግዶችን የመቀበል ዓቅም የለዎትም።»

« ንዱት ንዲህ ልትል ደፈርክ? ወደዚህ አምጣቸው ብዬሃለሁ!»

«አሁን ንጉሥ ሄሮድስ ሰዎችን ሊቀበላቸው ነው» ብሎ ጠባቂው ለአስተናጋጁ ነገረው።

ሄሮድስ ሽክ ባሉት ንግዶች ፊት ብቁ ሆኖ ለመ የት ቢሞክርም፣ ከዓቅሙ በላይ ሆነበት። ሕመሙና ጭካኔው አስጠሊ አድርገው ል፤ ለዓይኑ፣ ለጆሮው ለአፍንጫም የሚጸ ረር ሆነ።

« ዚሁ ምሜ ብ ገኙኝም፣ ተጠር ችሁ ዚህ በመምጣ ችሁ ኩራት ይሰማኛል። ተቀመጡ። ቀዝቀዝ የሚያደርጋችሁ አንድ ነገር ይምጣላችሁ?» አላቸው።

አገልጋዮች ቱምር፣ ለውዝ፣ ና ዘቢብ አመጡላቸው።

አሁን ቀልዱና ጨዋ ው ተቀንሶ ወደ ቁም ነገር ተገባ፡፡ «ሕፃኑ ንጉሥ» . . . «የአይሁዶቹ ንጉሥ» የሚሉ ቃላት በሄሮድስ አ ምሮ ገብተው ንደ በርበሬ አቃጠሉት፡፡ ሊቋቋመውም አልቻ ለም፡፡ ማወቅ አለበት፡፡

«የምትፈልጉት - ምን ነበረ?» ብሎ ጠየቃቸው ጠቢባኑን፡፡

«ሕፃን ንጉሥ መወለዱን ተረድተናል፣ የአይሁዶቹን ንጉሥ ማለ ችን ነው፡፡ ግርማዊነትዎ በጣም በመ መምዎ ወራሽ በማግ ኘትዎት ደስ ሳይልዎት አይቀርም፡፡

ከዚህ የከፋ ምን ይበሉት?

«ዳሩ ግን -ግን፣» ያለ ማሚው ሽማግሌ ንጉሥ ቁጭ ለማለት ሞከረ፡፡ ቀጠለና፣ «ስለዚህ ጉዳይ አልሰማሁም- በፍጹም አልሰማሁም፡፡ ማን ነው የነገራችሁ?» አላቸው፡፡

«የነገረን ግዚአብሔር ነው ብዬ አምናለሁ፣» አለ ጋስጳር፡፡ « ላቁ አምላክ፣ የ ርስዎም አምላክ በአንድ ደማቅ ኮከብ የመራ አሳይቶናል፡፡»

ሄሮድስ ተንቀጠቀጠ፡፡ የሚጥል በሽ የያዘው መሰለ፡፡ አንድ ጠባቂ በጐን በኩል መጣና የ ንቅልፍ ክኒን ሰጠው፡፡

ሰብአ ሰገሉ በሐፍረት ተያዩ፣ በሽተኛውን ንጉሥ ስለ መ ረበሻቸው ይቅር የጠየቁ ወጡ፡፡

ሄሮድስ፣ « ንዳትሄዱ! ንዴት - ንደ ሆነ - ንገሩኝ - » ብሎ ተነፈሰ፡፡

«ያነበብናቸው መጻሕፍት ልክ በዚሁ ወቅት ሕፃን ንጉሥ ይወለዳል ይላሉ፣» አሉት፡፡

«ሊቃነ ካህናቱና ጸሐፍትን ሁሉ ወደ ኔ አምጡልኝ! በአስቸኳይ!» በማለት ንጉሥ በአገልጋዮቹ ላይ አንባረቀባቸው፡፡



«ግርማዊነትሥ. . . » አለ አንዱ።

«ግርማዊነትሥ. . .» ብሎ ሌላውም ደገመ።

ሊቀ ካህናቱና ጸሐፍት ቀረቡ።

« ሺ፣ ንግዲህ ሂዱና የትንቢት መጻሕፍ ችሁን መርምሯቸው። የአይሁዶች ንጉሥ፣ ንዲሁም፣ መሢሕ፣ የሚለውን ተመልከቱ፤ ጐሽ፣ ዲያ ፈጠን በሉና ሂዱ!» አላቸው።

«ክቡራት ንግዶቼ፣ ስቲ ዘና በሉ፣» አለ ሄሮድስ፣ ንዳይቅለበለብ በጣም የተጠነቀቀ። «ስለ ሳይንሳዊ ግኝቶቻችሁ ስቲ አጫውቱኝ» አላቸው።

ጠቢባኑ ግን ከኮከቡ በቀር ስለ ሌላ ነገር ማሰብ አልቻሉም።

ሊቀ ካህናቱና ጸሐፍቱ ተመልሰው መጡ።



« ንግዶቹ ልክ ናቸው፣» አሉ። በመቀጠልም፣ «ቦ ው ግን ኢየሩሳሌም ሳይሆን ቤተ ልሔም ነው፣» አሉት።

«መልካም ነው፣ ክቡራት ንግዶቹ፣» አለ ሄሮድስ። «ስለ ጠየቃችሁኝ አመሰግናችኋለሁ። ወደ አገራችሁ ስትመለሱም በዚሁ በኩል ለፉ። ሕፃኑን ስከም ገኙት ድረስ ቦ ውን ፈልጉት፣ ኔም ሄጀ ለትንሹ ግርማዊ ሰግድለት ዘንድ ቦ ውን ንገሩኝ፣» አላቸው።

ጠቢባኑ በምስጋናና በ ላቅ አክብሮት ተሰናብተው ወደ ቤተ ልሔም አቀኑ።

ከዚህ በኋላ ሄሮድስ በጣም ተናደደ፤ ቀባጠረ፣ ጮኸ፣ ተንተባተ በም።

አስተናጋጁ፣ «ግርማዊነትዎ፣ ስው ንዲከተላቸው ናድርግ ንዴ?» ብሎ ጠየቀ።

«የለም! የለም! ሁሉን ንደ ጨለማ በምሥጢር ያዙት! ጨለማ!

ስለ ርሱ ካወራን አንዳንድ ደደቦች ሪኩን ይሰሙና ነገሩ ጥሩ አይሆንም። ትክክለኛውን ንጉሥ ማንም ንዲረሳው አልፈልግም - ኔ መሆኔን ማለቴ ነው፣ ላቁ ሄሮድስ! የኮከብ ተመራማሪዎ ቹን ተመልሰው መጥተው ንዲነግሩኝ አዝዤአቸዋለሁ። ከዛ በ ኋላ የማደርገውን ኔ አውቃለሁ። ከዚያ፣ ከዚያማ - የማደርገውን - ኔ - ኔ አውቃለሁ፣» አለ የተንተባተበ።

ወሬው በኢየሩሳሌም ሁሉ ተዳረሰ። ሰዎች ግን፣ የተናገሩት ስለ ሕፃኑ ሳይሆን፣ ስለ ሄሮድስ ነበር። አሁን ይሄ ጨካኝና ብድ ንጉሥ ምን ያደርግ ይሆን? አሁን ደግሞ የማን ጭንቅላት ተ ቀልቶ፣ ስንት ጭንቅላት ተቆርጦ ይንከባለል ይሆን?

ማንስ ተጠያቂ ይሆን? የኢየሩሳሌም ሰዎች ተረበሹ።

ሄሮድስ ደግሞ ተረበሸ። ሄሮድስ ጠቢባኑ ስኪመለሱ ድረስ መቆየት አቃተው። የጣቶቹን ከሲ መገጣጠሚያዎች አላመጠ።



3

ስሙም ኢየሱስ ይባላል

ዛሬ ሕፃኑ መሢሕ ከተወለደ ሰምንት ቀን ሆኖ ል። ይህ ቀን ደግሞ በቤተ ልሔም በሚገኘው ምኩራብ ውስጥ ልዩ ሥርዓት የሚከናወንበት ዕለት ነበር። ትናንሽ የአይሁድ ወንድ ሕፃናት ሁሉ ይህንን ሥርዓት ይፈጽሙ ነበር። ስከ ዛሬም ድረስ በዓለም ዙሪ ያ የሚገኙ ትናንሽ የአይሁድ ወንድ ሕፃናት ይህንን ሥርዓት ይፈጽሙ ል። ስምንተኛው ቀን ለሕፃኑ ስም የሚወጣበት ቀን ነው።

ማርያም ለሥነ ሥርዓቱ አከባበር ብላ ሕፃኑን አለባበሰችው፣ ዮሴፍ ደግሞ ከዛ ከተወለደበት ዋሻ አውጥቶ ወደ ምኩራብ ተ ሸክሞ ሊወስደው የጠበቀ ነበር።

ማርያም፣ «ዮሴፍ ስኪ አንዴ ቆይ፣ ትንሽ ምግብ ጨምሬ ማብላት አለብኝ። በሥነ ሥርዓቱ መሀል ንዲርበው አልፈልግም፣» አለችው።

ስለዚህ፣ ማርያም ለሕፃኑ ትንሽ ጨምራ ማጥባት ጀመረች። ማርያም ለ ርሱ የሚሆን ብዙ ምግብ ነበራት። ርሱም አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ክብደት ጨምሯል። መጨመሩ የ ወቀው ልጁ የፋፋ በመሄዱ ንጂ ማርያም በግርግሙ ውስጥ የመለኪያ ሚዛን ስለ ነበራት አይደለም።

«ዮሴፍ ነዚህን የሚያምሩ ክንዶቹን ተመልከ ቸው፣ ከበፊቱ አሁን ወፈር አላሉም? ፊቱ ደግሞ ድንቡሽቡሽ ብሎ ብርቱኳን መስሏል!» አለች።

ሕፃኑ መሢሕ ውብ የሆነ ትንሽ ልጅ ነበር።

ዮሴፍ በትዕግሥት ይጠብቅ ነበረ። መቼም አባቶች ሁልጊዜ ናቶችንና ሕፃናትን ንደ ጠበቁ ናቸው።

ማርያም ሕፃኑ ንዲያገሣ ካደረገች በኋላ፣ በፎጣ ጠቅልላ

ለዮሴፍ አቀበለችው። ከዚያም መጐናጸፊያዋን በትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ፣ መከናነቢያዋን ተከናነበችና ለመሄድ ዝግጁ ሆኑ።



የሚቈላለፉቸው በሮች አልነበሯቸውም። የዋሻው መግቢያ ለሚዳውም ለሰማዩም ክፍት ነበረ። ከ ንግዶች ማደሪያ ጥጉን ይዘው፣ ደብዛዛ ወደ ሆነው የክረምት ፀሐይ ወጡ። ከስምንት ቀናት በፊት ከናዝሬት ተነሥተው በደረሱ ጊዜ በሰው ብዛት ተ ጨናንቆ ወደ ነበረው ቅጥር ግቢ ደረሱ፤ ርሱን ተሻግረው ትንሽቱን ቤተ ልሔም ከተማን አልፈው ወደ ምኩራቡ ገቡ።

ዛው ለሕፃኑ ሥነ-ሥርዓቱን ያከናወነው፣ ቸርና ጨዋ የሆነው መምህር (ረቢ) የሕፃኑን ስም ጠየቀ።

«ኢየሱስ ይባላል፣» አለ ዮሴፍ « ርሱም ሕዝቡን ከ ጢአ ቸው ያድናቸዋል» የሚሉትን የመልአኩን ቃላት

ከትንፋሹ ሥር ደብቆ።

ሥርዓቱ በሚፈጸምበት ጊዜ ሕፃኑ ትንሽ አለቀሰ፣ ነገር ግን መምህሩ ለዮሴፍ ካሳቀፈው በኋላ ዝም አለ፣ ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደው።

ማርያምና ርሱ ለመሄድ የተዘጋጁ ሳለ፣ ዮሴፍ መምህሩን አመሰገነው።


«የመጣችሁት ከገሊላ ነው አይደል?» ሲል ጠየቃቸው መምህሩ። ቀጠለና፣ «በአነጋገራችሁ አወቅኋችሁ። ንዴት ወደ ቤተ ልሔም ልትመጡ ቻላችሁ ዲያ?» ሲል በድጋሚ ጠየቃቸው።

«ለቄጠራው ስንል፣» አለው ዮሴፍ። «ከዳዊት ሐረግ፣ ከዳዊት ቤተሰብ ነን። የመጣነውም ለሕዝቡ ቄጠራ ስንል ነው።»

«አዎ፣ ልክ ነው፣ ለሕዝብ ቄጠራ። ባለፈው ሳምንት ቤተ ልሔም ንዴት ተጨናንቃ ነበር መሰላችሁ። በዚህ ሳምንት ግን ጸጥ ብላለች። አብዛኞቹ ሰዎች አሁን ወደየአገራቸው ተመልሰዋል። ዘመድ ያላቸው ጥቂቶች ግን ጉብኝ ቸውን አራዝመዋል። ወደ ገሊላ ስትመለሱ ንግዲህ መልካም ጉዞ ይሁንላችሁ! ስለ ባለቤ ትህ የመንጻት ሥርዓትና ሕፃኑ ካህኑ ፊት ስለሚቀርብበት ቀን በኢየሩሳሌም የምትቆዩ ይመስለኛል። ከዚህ በፊት ከቤተ ልሔም መሄዱ ጥቅም ያለው አይመስለኝም፣ አለው ንዴ? ለመሆኑ ከወዳጆቻችሁ ዘንድ ነው ያረፋችሁት?» አለና መምህሩ ጠየቀ።

«የለም፣ አሁን ያለነው በግርግም ነው። በመጣን ጊዜ የነበረና የተሰጠን ቦ ይሄ ብቻ ነበር። አሁን ግን ሌላ ብናገኝ ደስ ይለን ነበር» አለው ዮሴፍ።

«አሁንማ ብዙ የሚከራዩ ትናንሽ ቦ ዎች አይጠፉም። ለምን አ ፈላልጉም? ሥራህ ምንድን ነው? ሥራስ ትፈልጋለህን?» አለ፣ መምህሩ ሊረዳቸው ፈልጎ።



« ኔ አናጢ ነኝ፣» አለ ዮሴፍ። «ለአናጢ የሚሆን ሥራ ምንጊዜም አለ። ላረፍንበት ስፍራ ባለቤት አንዳንድ ነገሮችን ስሠራለት ቆይቻለሁ። ለቤት ኪራያችንና ለምግባችን ችሎልን ቆይቷል።»

«መልካም፣» አለ ቸሩ መምህር። «አሁንም ሂድና በቤተ ልሔም ያለውን አናጢ ፈልገው። ስ ገኘውም ኔ ንደ ላክሁህ ንገረው፣ ርሱ በቂ ሥራ ይሰጥሃል። የሚሠራ ሥራ ንዳለው ሰምቻለሁ። ከምኩራቡ ወጥተህ ወደ ቀኝህ ዙር፣ የሥራ ቦ ውን አ ጣውም። የምትከራዩት ትንሽ ቤትም ሳይጠቁምህ አይቀርም።»

ዮሴፍ በድጋሚ መምህሩን አመሰገነው።

ከምኩራቡ የወጡ ሳለ፣ ዮሴፍ፣ «ማርያም፣ አንቺ ከ ኔ ጋር ትመጫለሽ፣ ወይስ መጀመሪያ ወደ ዋሻ ላድርስሽና ተመልሼ ብቻዬን ልሂድ?» አላት።

« ንዴ፣ የለም፣ ካንተ ጋር ሄዳለሁ!» አለችው።

«ትንሹ ኢየሱስ ከፊቱ የሚጠብቀው ንዴት ያለ ሥራ ነው!» አለች ማርያም የምኩራቡን ደረጃ የወጡ ሳለ። «ሕዝቡን ከ ጢአ ቸው ነፃ ማውጣት አለበት። ይሄ ለ ኔ ሊገባኝ አይችልም። መሢሕ መሆኑንና ሕዝቡን ንደሚመራ አውቃለሁ፣ ነገር ግን ከ ጢአ ቸው ደግሞ ነፃ ሊያወጣቸው ነው። መልአኩ ያለው ይህንን ነበረ፣» አለች ማርያም።

«አዎን፣» አለ ዮሴፍ፣ «መልአኩ ለ ኔም የነገረኝ ይህንኑ ነበር፦ ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ፣ ምክንያቱም ርሱ ሕዝቡን ከ ጢአ ቸው ነፃ ያወጣቸዋልና። ይሄ በሂደት የገባን ይሄዳል፣ ማርያም። ኛ አሁን ማድረግ ያለብን ያልገባንን ነገር ለ ግዚአብሔር ትተን፣ ልጁን መንከባከብና ማሳደግ ነው። የ ግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አልረሳነውም፣ ረስተነዋል ንዴ?» አላት።

« ንዴ፣ የለም። ያንን የረሳን አይደለም፣» አለችው ማርያም።

«መልካም፣ የመጀመሪያው ሥርዓ ችን ንግዲህ ዚህ ላይ አብቅቷል፣» አለ ዮሴፍ። «በመቀጠልም፣ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደን የቤተ መቅደሱን ሥርዓት ስክናከናውን ድረስ ዚሁ ተደላድለን መቆየት አለብን። ገና አምስት ሳምንት አለን፣ አይደል? ከዚህ በኋላ ወደ አገራችን ወደ ገሊላ ንሄዳለን፣» አለ።

«ለስድስት ሳምንት ሕፃን ልጅ ረጅም መንገድ ነው - 144 ኪሎ ሜትር ኮ ነው፣ ያም ሆነ ይህ በቀላል ዘዴ ንወጣዋለን፣ አይደል ንዴ?» አለች ማርያም።

አሁን ዮሴፍና ማርያም፣ ሕፃኑን ቅፈው፣ የአናጢውን ሰውዬ የሥራ ቦ የፈለጉ በመሄድ ላይ ናቸው። ሰብሰብ ብለው ይነጋገሩ በነበሩ ሰዎች አጠገብ አለፉ።



«አሁንም በቤተ ልሔም ንግዶች አሉ ለካ፣» አለች ማርያም። «በአለባበሳቸውና በአነጋገራቸው ይ ወቃሉ። አነጋገራቸውን ማዳመጥ ደስ ይለኛል!» አለች በመቀጠል።

« ንዴት፣ ቤተ ልሔም ኮ ከሰሜን ወደ ግብፅ በሚወስደው ቁልፍ በሆነው መንገድ ላይ ስላለች ዋነኛ ማረፊያ ስፍራ ነች፣» አላት ዮሴፍ። በመቀጠልም፣ «ቤተ ልሔም ሁልጊዜ ንግዶች የሚኖሯት ይመስለኛል።»

በአናጢው ቤት በደረሱ ጊዜ፣ ዮሴፍ የመምህሩን ስም መጥራቱ ተአምር ፈጠረ። « ንዴ ወዳጄ፣» አለው አናጢው ለዮሴፍ። «ለአንተ የሚሆን ብዙ ሥራ አለኝ። ለጥቂት ሳምን ት የምትኖርበት ትንሽ ቦ ምናልባት ትፈልግም ይሆናል፣ ትፈልጋለህ ንዴ? ንዳውም፣ የራሴ የሆነች ትንሽ ቤት አለችኝ፣ ጥቂት ጥገና ትፈልጋለች፣ ጠገንገን አድርገህ ብትኖርባት ውለ ንደ ዋልክልኝ ቄጥረዋለሁ። ከነሙሉ ዕቃዋ አከራያ ለሁ። ቆንጆ ቤት ናት። በሕዝብ ቄጠራ ጊዜ ግን የተከራይዋት ሰዎች ትንሽ አበላሽተዋ ል። አንዳንድ የአናጢ ሥራ

ንደሚያስፈልጋት ተገንዝቤያለሁ፣ አንዳንዶቹ ዕቃዎችና በሮቹ መጠገን ይፈልጋሉ። ዛው ሄደህ የዋለህ።

« ዛ በነዛ ብትኖርስ? ቢያንስ ቢያንስ ላደረግኸው አንዳንድ ጥገና ማካካሻ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ በሥራ ቦ ለአንተ የሚሆን ሥራ አለኝ። ለዚህ ደግሞ ከፍልሃለሁ፣ የቀለብ መሸመቻ ይሆንሃል። ንዴት ነው? ምን ይመስልሃል?» አለው።

ዮሴፍና ማርያም ተያዩ። የማርያም ዓይኖች የምስጋና ዕንባ ቋጠሩ።

«በጣም ጥሩ ነው። ግዚአብሔር ይስጥልን፣» አለ ዮሴፍ።

« ዲያ መቼ ትገባላችሁ?» አለ አናጢው። በመቀጠልም፣ «አሁን? ንዲረዳችሁ ልጅ ልላክላችሁ?» አለ።

ስለዚህም ማርያም፣ ዮሴፍና ሕፃኑ ኢየሱስ ንዲሁም ትንሹ አህያቸውም ጭምር ቤቱን ገቡበት። ጥሩ ቤት ነበር።

«የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ፣ በሚያስፈልገን ጊዜ አገኘን!» አለች ማርያም።



4

«ኑና መሚሑን ዩት!»

ሳምን ቱ አለፉ። ዮሴፍ በቤተ ልሔም ብዙ ሥራ ነበረው፣ ደስተኛም ነበር። ማርያም ደግሞ የምትወድደውን ልጇን መንከባከብ ደስ ይላት ነበር። ፀሐይ ሞቀው፣ ትዘምርለት፣ ትመግበው፣ ንዲሁም ጥበው ነበር። ደግሞም በትንሿ ጣቱና በ ግሩ አውራ ጣት የነካካች ጫወተው ነበር። ደስተኛም ነበ ረች።

ሕፃኑ ኢየሱስ አሁን የስድስት ሳምንት ልጅ ሆኗል። አምስት ኪሎ ሜትር ርቆ ወደሚገኘው፣ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መቅደስ የመሄጃው ጊዜ አሁን ነበር። ሕፃኑ ለ ግዚአብሔር መሰጠት ነበረበት። ስድስት ሳምንት የሆናቸው ልጆች ናቶቻቸው ንደሚያደርጉት ሁሉ፣ ናቱም ማርያም በመንጻት ሥርዓት ውስጥ ማለፍ ነበረባት፣ ከዚህ ሥርዓት በኋላ ናቶቹ በቤተ መቅደሱ ንዲሁም በምኩራቡ ውስጥ በሚከናወነው ጸሎትና ስብከት ሊካፈሉ ይችሉ ነበር።

ሥርዓቱ ለ ግዚአብሔር የሚቀርብ ምስጋና ነበር፣ «ሕፃኑ ከተ ወለደ በኋላ ጤናማና ብርቱ በመሆኑ አመሰግንሃለሁ!» የሚል ነበር።

አንድ ጧት ማርያም፣ ዮሴፍና ሕፃኑ ኢየሱስ ከትንሹ አህያቸው ጋር ሆነው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ተነሡ። ማርያም ረኸቦሙን መንገድ የተጓዘችው ኢየሱስን ቅፋ በአህያው ላይ ተፈናጥጣ ነበር።

በዚያን ቀን ሌሎች ናቶችና ሕፃናት በቤተ መቅደሱ ውስጥ ተ ገኝተው ነበር። ሀብ ም የሆኑት ናቶች የበግ መሥዋዕት አቀረቡ። ድሆች የሆኑቱ ደግሞ ንደ ዓቅማቸው ለማመስገን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ጫጨቶችን ማቅረብ ይችሉ ነበር። ማርያም፣ ዮሴፍ ከቤተ መቅደሱ ገብቶ ያመጣላት ሁለት ጫጨት ርግቦችን (ዋኖሶችን) ለመሥዋዕት አቀረበች። በዚያ ቀን ማርያም ከሌሎቹ መጫት ናቶች ጋር በአምልኮ ሥርዓት ላይ

ለመገኘት ጤናማና ብቁ ነሽ ተባለች።



አሁን ደግሞ ማርያም ከዮሴፍ ጋር ሆና ወደ ሌላ ሥርዓት ወደሚፈጸምበት ቦ ሄደች። ይኸውም ሕፃኑን የተቀደሰ ለማድ ረግና ለ ግዚአብሔር ለማቅረብ ነበር። ዮሴፍና ማርያም በሥርዓቱ ክንዋኔ በስሜት ተነቃቁ። ስቲ አስቡት ግዚአብሔር ለ ግዚአብሔር ሲሰጥ!

ካህኑ፣ ሕፃኑን ከዮሴፍ ጅ ተቀብሎ መረመረው (ንደ ዶክተ ር)። ሕፃኑ ፍጹም ነበር።

ካህኑ፣ ሕፃኑን ኢየሱስን ለዮሴፍ መልሶ ንደ ሰጠው አንድ ሽማግሌ ወደ ፊት መጣና ማንም ሳያውቅ ሕፃኑን ወስዶ ቀፈው! ይህን ሲያደርግ ማንም አላስቆመውም።

ለጊዜው ማርያም ተደናገጠች። ካህኑን ትኩር ብላ አየችው። ፈገግ ብሎ ትከሻውን ነቅ ነቅ ያደረገ፣ «አይዞሽ፣ ሽማግሌው ስምዖን የሚያስፈራ አይደለም! ተይው። የሚገዳ አይደለም። ልዩ ሕፃን ሲያገኝ ደስ ይለዋል። ይህንን ለዓመት አድጎ ል። ሁሌ ንደ ቋመጠ ነው። ከመሞቱ በፊት መሣሉን ንደሚያይ ግዚአብሔር ንደ ገለጠለት ይናገራል። ስለዚህ ስምዖን ሕፃኑን አይገዳውም። አሁን ይቅር ይደረግልኝ፣» አለና ካህኑ ሌሎቹን ለማገልገል ፊቱን አዞረ።



ማርያም ና ዮሴፍ ንደ ሆነ ውድ ከሆነው ሕፃን ዓይናቸውን አልነቀሉም። የሚገዳም ይሁን አይሁን፣ ሽማግሌውን በቅርብ መከ ተል ይኖርባቸዋል።

የሽማግሌውን ፊት ባያችሁት ኖሮ። የሚያበራ ነበር። የደስ ንባ በጉንጮቹ ይወርድ ነበር። አዳምጡት! «ጌ ሆይ፣ አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተኝ። በቅርብ ቢሆን ግድ የለኝም። መድ ኑን አይቼዋለሁና በቃኝ። የሰጠኸኝ ተስፋ ይኸውና ተ ፈጽሟል። ሕዝብ ሁሉ ያዩት ዘንድ ያዘጋጀኸውን ማዳንህን አይቸዋለሁ፣ ርሱም ለአሕዛብ ብርሃንን ለ ስራኤል ሕዝብ ደግሞ ክብርን የሚያመጣ ነው።»

ማርያም ምን ያህል ትደሰት! ግዚአብሔር ለሽማግሌው ነግሮት ነበር ለካ! ሊነግረው የሚችለው ግዚአብሔር ብቻ ነው። የ ርሷ ኢየሱስ ለካህኑ ተራ ሕፃን ንደ ነበረ ግልጥ ነው። ለሽማግሌው ግን ሕፃኑ መሢሑ ነበር። ሕፃኑ መሢሑ ነበር። ሕፃኑ ማን ንደ ነበረ ግዚአብሔር ለስምዖን ነግሮት ነበር!

ስምዖን ደስ በሚል ሁኔ የሕፃኑን ፊት ትኩር ብሎ ሲመለከተ ው ከቆየ በኋላ፣ ማርያምና ዮሴፍን ባረካቸው። ማርያምንም ንዲህ አላት፡- «በዚህ ልጅ ፊት የሰዎች ውነተኛ ማንነት ይ ያል። ርሱ ባለበት የሚደበቅ ሐሰት የለም። ርሱን የሚቀበሉ ደ ንነትን ያገኛሉ። ርሱን የሚቃወሙ ደግሞ ይጠፋሉ። ይጠሉ ልም። አንችም ልክ ልብሽ በሰይፍ የተወጋ ያህል ትሠቃያለሽ።»

ይህ ለማርያም አዲስ ነገር ሆነባት። ሕፃኑን ከሽማግሌው ስምዖን የተቀበለችው ያለ በጉዳዩ ማሰብ ጀመረች። መሢሑን በማሳደግ፣ ነገር ሁሉ ደስ ንደሚሆንላት አስባው ይሆን?



ከዚህ በኋላ ደግሞ ወዲያውኑ አንዲት በጣም አሮጊት ግሮ ን የጮተተች ወደ ነርሱ መጣች። ይህች አሮጊት ሴት ነቢይቷ ሐና ነበረች። «መሢሁ ዚህ ንዳለ ግዚአብሔር ነግሮኛል። ላየው ችላለሁን?» አለች።

ማርያም ያንን ገራምና ውብ የሆነውን የአሮጊቷን ፊት አንዴ አየት አደረገችና ሐና ሕፃኑን ንድ ቅፍ ፈቀደችላት። ሐና ሕፃኑን ትኩር ብላ ስ የው፣ ፊቷ አበራ። የትንሹን ሕፃን ፊት በደንብ አጠናችው።

«ጌ አምላኬ!» አለች፤ በመቀጠልም፣ « ስከዚች ቀን ድረስ ኖሬ፣ ርሱን

ለማየት በመብቃቱ ከሁሉ ጠቃሚ ነገርን አገኘሁ!»

ሐና ሕፃኑን ለማርያም መልሳ ሰጠቻት። «አንቺ የ ደልኽ ሴት ነሽ!» አለቻት። « ግዚአብሔር ይባርክሽ! የዛሬ ስልሳ ዓመት ባለቤቱ ሲሞት ኔ ወጣት ነበርኩኝ። ከዛ ንክትክት አልኩኝ። ግዚአብሔርን በማገልገል መጽናናትን ፈለግሁ። ያኔ ወደዚህ ቤተ መቅደስ ንደ መጣሁ ነኝ፣ አሁን ከመጣሁ ከስልሳ ዓመት በላይ ሆኖኛል። 'ነቢይቷ ሐና' ብለው ይጠሩኛል። ነዚህን ዓመ ት ያሳለፍኳቸው ሌትና ቀን፣ ለረኻቦም ሰዓ ት በመጸለይ ነው። ወዳጆቼ <ሐና፣ ተይ፣ ኛ ጋር ነይ። ተደሰቺ> ይሉኛል። ዛሬ ግን የደስ ጽዋዬ ሞልቷል፤ መሢሑን አይቼዋለሁና!» አለች ሐና።



በቤተ መቅደስ ቆመው ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ሐና መንገር ጀመረች። «ኑና መሢሑን ዩት!» አለቻቸው።

ሰዎች መጥተው ዮሴፍን አዩት። የለም፣ ዮሴፍ ሊሆን አይችልም። ርሱ - መሢሑ? መሢሕ ኮ ዋቂ ነው፣ ላቅ የሠራዊት መሪ ነው። «የት ነው ዲያ?» አሉ።

አንዳንዶቹ ሕፃኑን አዩት። «ደስ የሚል ትንሽ ልጅ! ደስ የሚል ሕፃን!» ምንም ፍንጭ አ ል ነ በ ራ ቸ ው ም ። ግዚአብሔር ለ ነርሱ ሊነግራቸው አልፈለገም።

ግዚአብሔር ነግሮአቸው ነበረና ሐና ና ስምዖን ግን አውቀው ነበር።

ከቤተ መቅዱስ ወደ ቤተ ልሔም በመመለስ ላይ ያሉ ማርያምና ዮሴፍ ንደገና ጉዳዩን በማንሣት ይነጋገሩ ነበር።

«ደግ ነው፣ ማርያም፣ አሁን በፈለገው ቀን ወደ አገራችን ናዝሬት መመለስ ንችላለን፣ በመጀመሪያ ግን አንድ ሁለት ሥራ ዎችን ለአናጢው ጨርሼለት መሄድ ፈልጋለሁ። ርሱ ለ ኛ ደግ ሰው አይደለምን? በአንድ ወይም በሁለት ቀን ውስጥ ሠራዋለሁ። ከዚህ በኋላ ወደ አገራችን ወደ ናዝሬት ንመለሳለን።»

ናዝሬትን ከማየ ቸው በፊት ብዙ አደጋ መኖሩን ዮሴፍ አላወቀም ነበር።



5

«አይተነዋል!»

« ኔ በበኩሌ ከዚያ መውጣ ችን ደስ ብሎኛል! ንዴት ያለ ጣጣ ነው ይሄ!» አለ ጋስጳር ርሱና ጓደኞቹ ከሄሮድስ ቤተ



መንግሥት የወጡ ሳለ። ጋስጳር፣ መልቂዮር ና ቤልጣሳር፣ ሁሉም ከምሥራቅ የመጡ ጠቢባን ሲሆኑ፣ ከቤተ መንግሥቱ ወጥተው በኢየሩሳሌም በሮች በኩል አልፈው ጕዛቸውን ሊቀጥሉ ተዘጋጅተው ነበር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከግመሎቻቸውና ከአሽከሮቻቸው ጋር ተገናኝተው ወደ ቤተ ልሔም ያመራሉ።

«አሁን ሁሉንም ነገር አይተነዋል። ንዴት ያለ ጨካኝ፣ አውሬ ገዢ ነው ባካችሁ! ሄሮድስ የሚፈራና የሚጠላ፣ የሚያንገሸግሽና አስጠሊ ንዲሁም በሐሜት ኝኩ የተተፋ ንጉሥ ነው። ርሱ ባለበት ሕዛኑ መሚሕ አለመወለዱ ትልቅ ዕድል ወይም በረከት

ነው! ምስኪኑ ሕፃን ሁለት ደቂቃ ንኳ ንዲኖር አያደርገውም ነበር። ዳሩ ግን፣ አሁን ኑ፤ በቤተ ልሔም የተወለደውን ሕፃን፣ ውነተኛውን የአይሁድ ንጉሥ የሆነውን ንፈልገው። ቤተ ልሔ ም ከዚህ ሩቅ አይደለችም።»

ብዙ ሳይቆይ መሸ። ኮከቡ ንደገና ወጣ፣ ጠቢባኑ ርሱን ተ ከትለው ወደ ቤተ ልሔም ተጓዙ።

አሁን ነዚህ ያጌጡ ብዙ ግመሎች፣ ጠቢባኑ ና ተከ ዮቻ ቸው ወደ ቤተ ልሔም በመጓዝ ላይ ያሉ ማንም አያያቸውም ብሎ ማለቱ ዘበት ነው። ደ ና፣ መ የት ይ ዩ፣ ነገር ግን፣ ናንተ ንደም ስቡት በጣምም አይደለም። የተጓዙት የንግድ ምልልስ የሚደረግበትን መንገድ ይዘው ነበር። ማንም ሰው፣ የትም ይሂድ የት፣ በዚሁ የንግድ መንገድ ማለፉ አይቀሬ ነው። ሌላ መሄጃ መንገድ አልነበረም - አይሮፕላን የለ፣ ባቡር የለ፣ መኪና የለ ወይም አውቶቡስ። ስለዚህ ምንም የዘነጡ ወይም ዋቂ ሰ ዎች ቢሆኑ፣ በዚሁ የንግድ መስመር ይጓዙ ነበር።

«የቤተ ልሔም ርቀት፣ ስምንት ኪሎ ሜትር ነው ያሉት? ይሁን ንጂ፣ ትክክለኛውን ሕፃን የምናገኘው ንዴት ነው? ከ ርሱ ሌላ ቤተ ልሔም ውስጥ ብዙ ሕፃናት ይኖራሉ።» መልቂዮር የሚለው ልክ ነው።

« ላቁ ግዚአብሔር ንግዲህ ዚሁ ድረስ መርቶናል። ርሱው ያሳየናል፣» አለ ጋስጳር። በመቀጠልም፣ «ኮከቡም ይመራናል ብዬ አምናለሁ» አለ።

በ ርግጥም ኮከቡ መራቸው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ «በምሥራቅ ያዩት ኮከብ፣» ይላል። «ሕፃኑ በነበረበት ቦ ላይ ስኪቆም ድረስ ከፊት ከፊ ቸው የሄደ ይመራቸው ነበር።»

ጋስጳር፣ መልቂዮርና ቤልጣሳር በደስ ተዋጡ። ሕፃኑ የአይሁድ ንጉሥ የነበረበትን ቦ አገኙት።

«ጉብኝ ችን ግን በጨለማ መሆን የለበትም፣» አለ ጋስጳር። «በጧት ስጦ ችንን ይዘን ሄደን ንስግደለ ለን» አለ በመቀጠል።

«በቤተ ልሔም አንድ ጥሩ የ ንግዶች ማረፊያ ንዳለ ሰምቻ ለሁ፣» አለ መልቂዮር። በመቀጠልም፣ «ምርጫዬ በ ንግዶቹ ማ ረፊያ ማደር ነው። ውጭ መስፈሩ በዝቶብናል። አሽከሮቹ ውጭ ሰፍረው ንስሶቹን ሊጠብቁ ይችላሉ። ኛ ግን በ ንግዶች ማደሪ ያ ንደር።» ሁሉም በአሳቡ ተስማሙና ጋስጳር የ ንግዶች ማ ረፊያውን በር አንኳኳ።

«ጌቶቼ፣ በ ኔ የ ንግዶች ማረፊያ ማደር መፈለጋችሁ ለ ኔ ክብር ነው፣» ሲል የ ንግዶች ተቀባዩ በአክብሮት ተቀበላቸው። በመቀጠልም፣ «በሚገባ! ንዳውም በደንብ ንዲመቻችሁ ለማድ ረግ ደስ ዬ ላቅ ይሆናል። ደስ የሚላችሁን ምግብ ዘዙ። ኔ ራሴ ተከ ትዬ ንዲቀርብላችሁ አደርጋለሁ፣» አላቸው።

ስለዚህ፣ ጠቢባኑ ዛው ዐረፉ።

ቤልጣሳር ደግሞ ስለ ሕፃኑ ንደሚጠይቅው ለጓደኞቹ ነገራቸው።

«አያስፈልግም፣» አለው ጋስጳር። « ግዚአብሔር ሁሉን ነገር ያሳየናል፣» አላቸው።

ንግዳ ተቀባዩ ቀይ ምንጣፍ አነጠፈ። ገና ምንጣፉን ያመቻቸ ሽርጉድ በማለት ላይ ነበር። «ጌቶቼ፣ ልጠይቃችሁ ፍቀዱልኝና፣ ወደዚህ ምን ግር ጣላችሁ? ወደ ግብፅ የሄዳችሁ ነውን?» አለና ጠየቃቸው።

«አይደለም፣» አለ ጋስጳር። «መድረሻችን ንኳ ዚሁ ቤተ ልሔም ነው።»

« ውነት? ደፈርህ አትበሉኝና ወደ ቤተ ልሔም ለምን ጉዳይ መጣችሁ?» አለ ንግዳ ተቀባዩ ለማወቅ ጓጉቶ።

«የመጣነው የአይሁዶቹን መሢሕ ፈልገን ነው።»

«አሃ፣ አዎን፣ አዎን፣ ሁላችንም መሢሑን በመፈለግ ላይ ነን፣» አለ ንግዳ ተቀባዩ። በመቀጠልም፣ «ሲመጣ ደስ ይለናል። በሮም የተገዛን ነው። ሁላችንም ንጠላዋለን። የሕዝቡ ቁጠራ ዚህ ሲካሄድ ባያችሁ። ያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ መቁጠር ነበ ረበት። አቤት ሕዝብ መብዛቱ! መሢሑ ሲመጣ ደስ ውንም

አንችለውም። ንደሚመጣ ናውቃለን፣ ነገር ግን ጌቶቹ፣ ርሱ ኮ ዲያ ገና ዚህ አልመጣም።»

« ዚህ ነው፣ በቤተ ልሔም ነው ያለው፣» አለ ጋስጳር ቀበል አድርጎ። ቀጥሎም፣ «መጻሕፍት ይናገራሉ፣ በተጨማሪም፣ ኮከቡን አይተነዋል። ብዙ ኪሎ ሜትሮች ተከትለነዋል፣ ወደ ቤተ ልሔም መርቶ አምጥቶናል፣» አለው።

« 'ኮከብ' ነው ያልከው? 'ኮከብ'?»

«አዎን። ኮከብ አላየህም? አንድ ደማቅና ውብ የሆነ ኮከብ፣ ከሌሎቹ ተለቅ ያለ? ፈጽሞ አላየሁትም ንዳትለኝ ብቻ!» አለ ጋስጳር፣ ንግዳ ተቀባዩ ኮከቡን አለማየቱን ማመን ተስኖት።

«ኮከብ? አሁን ትዝ ብሎኛል፣ በቅርቡ አንድ ልዩ ደማቅ ኮከብ በሰማይ ይታይ ነበር። መጀመሪያ ሲ ይ ሰው ሁሉ ስለ ርሱ ያነሣ ይነጋገር ነበር፣ አሁን ግን የሚያነሣውም የለም። በመጀመሪያ የ የበት ቀን መቼ ንደ ሆነ ንኳ አሁን ላስ ውሰው አልችልም። አዎ፣ አሁን ትዝ አለኝ፣ በሕዝቡ ቁጠራ ጊዜ መሰለኝ። አሁን ግን ስለ ርሱ የሚያነሣም የለም። የዓለም ነገር ንዴት ንደ ሆነ ውቁ የለ፣ ጌቶች። ብዙ ነገሮች ብቅ ይሉና ለጊዜው ብርቅ ይሆኑና ሰው ያደንቃቸዋል፣ ከጊዜ በኋላ ይለመዱና መወራቱ ይቀራል። የኮኮቡ ነገር ለ ኛ ንደዛው ነው። ለ ናንተ ግን - » አለ አሳቡን ሳይቋጭ።



«ለ ኛማ፣ ኮኮቡ የ ግዚአብሔር መል ክት ነው!» አለ ጋስጳር፣ በ ንግዳ ተቀባዩ ንግግር በመገረም። በመቀጠልም፣ «መሢሑ ንደ መጣና በቤተ ልሔም ንዳለ የሚያመለክት ከ ግዚአብሔር የተላከ መል ክት ነው። መጻሕፍትም ይህንን ያ

ረጋግጣሉ። መሢሑ አሁን በቅርብ የተወለደው ሕፃን ነው። የመጣነው ርሱን ፍለጋ ነው።»

« ንግዲህ ልጁን ላፈላልግላችሁ። ስቲ ቆዩኝ፣ አሥ፣ በቅርቡ የወለደችው ሴት ማን ትሆን?» አለና ንግዳ ተቀባዩ ትንሽ ጊዜ አሰበ። « ንዴ ልክ ነው፣ አለች- አሥን ሣራ፣ ና ራሔል- ንዲሁም ዮዲት፤ የሚበጀው ግን በምኩራቡ ያሉትን ሰዎች መጠየቁ ነው። ዛ ያለው ጸሐፊ በቤተ ልሔም የተወለዱትን ሕፃናት ሁሉ ሊነግራችሁ ይችላል፣» አለ።

« ኛንማ ግዚአብሔር በኮከቡ አማካኝነት መርቶናል፣» አለ ጋስጳር።

«ደግ፣ ንግዲህ ራሳችሁ ማየት ትችላላችሁ ጌቶቼ፣» አለ ንግዳ ተቀባዩ።



ጋስጳርና ጓደኞቹ ንደገና ኮኮቡን ለማየት ወደ ውጭ ወጡ። ጮራው በተለይ ወደ አንዲት ቤት ያመለከተ መሆኑን ሦስቱም ተ ስማሙበት። ነገ ወደዚያች ቤት ይሄዳሉ። ሕፃኑ ዚያች ቤት ውስጥ መኖሩን ፍጹም ርግጠኞች ሆነዋል።

በዚያው፣ ለማወቅ የጓጓው የ ንግዶች ተቀባዩ ፍለጋውን

አጠናክሮ ነበረ። በቤተ ልሔም ዙሪያ የተወለዱት ሕፃናት የት የት ንዳሉ አጣራ። በስም ዝርዝሩ ውስጥ ስሙ ቢገኝም፣ በ ርሱ ግርግም የተወለደውን ሕፃን ግን ከቁጥር ውስጥ አላስገባውም። የተ መዘገበው «ኢየሱስ» ተብሎ ነበር።

በማግሥቱ ጧት፣ ከምሥራቅ የመጡት ጠቢባን፣ በኮከቡ መሪነት ፍጹም ርግጠኞች በመሆን፣ ስጦ ዎቻቸውን ይዘው ካደሩበት የ ንግዶች ማረፊያ ተነሥተው ወደዚያች ቤት አመሩ።

በዛም፣ ትንሹን ልጅ ከ ናቱ ጋር ሆኖ አገኙት። ለደስ ቸው ድንበር አልነበረውም። ዮሴፍም ዛው ነበረ። ማርያምና ዮሴፍ ወደ አገራቸው ወደ ናዝሬት ለመመለስ ይዘጋጁ ነበር።

ማርያምና ዮሴፍ ንደ ነዚህ ያሉ መኳንንቶችና ላላቅ ሰዎች ሊጠይቋቸው መጥተው ሲያዩ ከመገረም በቀር ምንም ሊናገሩ አልቻ ሉም።



«የመጣነው የአይሁዶች ንጉሥ ሆኖ ለተወለደው ‘መሢሕ’ ልንሰግድለት ነው» አሉ በትሕትና።

ለ ጌ ላ ት ወ ሰ ወ ሰ ቅ አላስፈለገም። ነዚህ ጉጉና የተከበሩ ተመራማሪዎች በመጨረሻ በሕፃኑ መሢሕ ፊት ቀረቡ። የወርቅ፣ የዕ ጣንና የከርቤ ስጦ ዎቻ ቸውን ያበረከቱ ተንበ ረከከው ከልባቸው ለሕፃኑ ሰገዱ። ልባቸውን በ ግዚአብሔር ፊት ባደ

አድርገው አቀረቡ። በጋስጳር ጉንጮች ላይ ንባ ፈሰሰ፣ በመጨረሻ ግዚአብሔርን አግኝቶ ልና።


ጠቢባኑ ለሕፃኑ የሰገዱ ረጅም ጊዜ ቆዩ። ግዚአብሔርንም ንዳገኙት አወቁ።

ማርያምና ዮሴፍ ምንም አልተናገሩም። አንዳንድ ጊዜያት ቃላትን ንኳ የማያናግሩ የተቀደሱ ናቸው። ማርያም በደስ ተ ሞላች። ግዚአብሔር ነዚህ ሰዎች ብዙ ኪሎ ሜትሮች ከቤ ቸው ርቀው፣ ከ ላቁ ምድረበዳ ወዲያ ቢሆኑም፣ ስለ ልጁ መወለድ ነገራቸው። ደማቁ ኮከብ ያንን ሁሉ መንገድ መራቸው። ማርያም ደግሞ በልቧ ውስጥ የሚቀመጥ ሌላ ትዝ አገኘች።



ንግዶቹ ሕፃኑን ለማግኘት ባደረጉት ፍለጋ ምን ላይ ንደ ደረሱ ለማወቅ ከሁሉ ጓጉቶ የነበረው የ ንግዳ ተቀባዩ ነበረ።

«የትኛው ሕፃን ነበረ?» ሲል ጠየቀ።



ጠቢባኑ፣ ዓለም አምቃ ከያዘቻቸው ምሥጢራት ውስጥ አንድ ነገር የጨበጡ መሰሉ። ፈነደቁም። ፊቶቻቸው አበሩ። ዓይኖቻቸው አርቀው ይመለከቱ ነበር።

«የትኛው ሕፃን ነበረ፣ ጌቶቹ?» አለና ጠየቀ የ ንግዳ ተቀባዩ በድጋሚ።

«አቤት ንዴት ያምራል? ነጸብራቁ ከ ርሱ ሲወጣ ተሰማኝ። አቤት ንዴት ያለ ገጠመኝ ነው!»

«የትኛው ነበረ፣ ጌቶቹ?» ጠቢባኑ ግን የ ንግዶች ተቀባዩን ከቁብ አልቆጠሩትም ነበር።

« ናቱ በሕዝቡ ቁጠራ ጊዜ ግርግም ውስጥ በበረት መወለዱን አልተናገረችምን? የትም ይሁን የት፣ ኛ አይተነዋል፣ መሢሑን! የልዑል ግዚአብሔርን ልጅ!»

«'ግርግም' ነበረ ነው ያልከው? ግርግም? የ ኔ ግርግም- ርሱ በ ኔ ግርግም ተወለደ፣ ኔ ሳላውቀው? ነገ ራሴ ሄጄ ፈልገዋለሁ፣» አለ የ ንግዳ ተቀባዩ።

ጠቢባኑ ለመሄድ ቸኮሉ፣ ወደ አገራቸው ለመመለስ። አሁን ተ ልዕኳቸው ተከናውኗል። ያውም በአመርቂ ሁኔ ። ዳሩ ግን፣



ከመጓዛቸው በፊት ትንሽ ማረፍ ነበረባቸውና ዐረፍም አሉ። ተኙ።

ጋስጳር ነቃ። «አይቼዋለሁ! . . . አይቼዋለሁ! . . . አዎን፣ አይቼዋለሁ። አናግሮኛል።»

«ምንድን ነው ርሱ፣ ጋስጳር?»

« ግዚአብሔር በሕልሜ፣ <ወደ ኢየሩሳሌም ንዳትመለሱ! ለሄሮድስ ንዳትነግሩት! ሕፃኑን ሊጎዳው አስቧልና ወደ አገራችሁ በሌላ መንገድ ሂዱ! ብሎኛል> አለ።»

«ግን ኮ ሄሮድስ ይናደድብናል። ያ ለልነው ይመስለዋል። የተጫወትንበትም ይመስለዋል፤ ያብዳል።»

«ማበድ አለበት!» አለ ጋስጳር። «በዛ ውብ ሕፃን - መሢሕ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ተጠያቂዎች መሆን አንችልም፣» አለ ጋስጳር በመቀጠል።

ቤልጣሳርም ሕልም አይቶ ነበርና በነቃ ጊዜ ወከ። ርሱም ሕልም አይቶ ነበር።

«በሌላ መንገድ ወደ አገራችን መመለስ አለብን፣» አለ። ቀጥሎ፣ «ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ንደ ፈለገ በሕልሜ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል። ቶሎ ንሂድ!» አለ።

ስለዚህ፣ ሰብአ ሰገሎቹ በሌላ መንገድ ወደ ትውልድ አገራቸው ተመለሱ።

ማርያምና ዮሴፍም ወደ አገራቸው ወደ ናዝሬት ለመሄድ ዕቃቸውን ያዘጋጁ ሳለ፣ ስለ ሰብአ ሰገሎቹ ጉብኝት በመገረም ይነጋገሩ ነበር። አሁን ከጓዛቸው ጋር የሚጨምሯቸው ሦስት በጣም ውድ የሆኑ ጥቅልሎች አሉ፡- ነርሱም ዕጣንና ከርቤ የያዙ ጥቅልሎች ናቸው። (ከርቤ ከሽቶዎች ጋር ተጨምሮ ለመዓዛ

የሚጠቅም ቅመም ነው)። ነዚህ ሦስቱ በጣም ውድ ዋጋ ያላቸው ነገሮች ናቸው።

በመጨረሻም፣ በማግስቱ ጧት ለሚደረገው ጉዞ ሁሉም ነገር ዝግጁ ሆኖ ወደ መኝ ቸው ሄዱ።

ኩለ ሌሊት ሆኖ ነበር። ዮሴፍ፣ ንድትነቃ ማርያምን ነቀነቃት። «ቶሎ በይ! ቶሎ በይ! ከዚህ ቶሎ ብለን መውጣት አለብን። ቶሎ! ጊዜ የለንም ቶሎ፣» አላት።

«ዮሴፍ፣ ምንድን ነው ችግሩ?» አለች ማርያም አልጋ ላይ ንዳለች፣ ደንዝዛ።

«ሕልም አየሁ፣ ማስጠንቀቂያ። ሄሮድስ ሕፃኑን ለመግደል ይፈልጋል። ሕፃኑን ሊገድለው ነው። መልአክ ነገረኝ። ዮሴፍ፣ ፈጥናችሁ ውጡ! አለኝ ።» «<ቶሎ!>»

«ዕቃችንን ንደ ሆነ አስረናል። ልብስሽን ለባብሺ፣ ማርያም። አህያውን ስክፈ ና ዕቃዎቹን ስክጭን ድረስ አንቺ የተኛውን ሕፃን ቀፊ።»



«ዮሴፍ፣ ወዴት ነው የምንሄደው?»

«ኡስ! . . . ኡስ! . . . ኡስ! ነይ ንግዲህ! በማለዳ መንገዱን ደ ና አድርገን ናጋምሰዋለን፣» አላት።

በአጋጣሚ፣ ጭልም ያለ ሌሊት ነበረ። ላቁ ኮከብ ጠፍቷል። ማርያም የጉዞ መጐናጸፊያዋን ደርባለች፣ መከናነቢያዋንም ራሷ ላይ አጣፍ ለች። ጧት ወደ ናዝሬት ለመጓዝ ነገሮች ሁሉ ተ ዘጋጅተው ቆይተዋል። ዕቃው ሁሉ ለመያዝ ቀላል ወይም ምቹ መሆኑ በጀ። ማርያም አህያው ላይ ስትፈናጠጥ ዮሴፍ ረዳት፣ ልጁንም አቀበላት። ልጁን ጠበቅ አድርጋ ያዘችው። ወዴት ይሆን የሚሄዱት? ርሷም ግራ ገብቷ ል። ዮሴፍ አህያውን የመራ ዋናውን መንገድ አስያዘውና ወደ ደቡብ ግብፅ አመሩ።

በማግሥቱ ጧት፣ ንግዳ ተቀባዩ፣ ሦስት የ ወቁ ንግዶች በ ርሱ የ ንግዳ ማረፊያ በማደራቸው ክብር ተሰምቶት ፊቱ በደስ የበራ፣ የተንገበገበለትን ሕፃን ለመፈለግ ወጣ። በደረሰ ጊዜ ግን ቤቱ ባዶ ሆነ አገኘው። ተሳስቶ መሆን አለበት። ወደሚቀጥለው በር ሄደ። «ሰዎቹ ወደ አገራቸው ወደ ናዝሬት ንደሚሄዱ ተናግረው ነበር። ስለዚህ ሳይሄዱ አይቀሩም፣» አሉት።

ስለዚህ የ ንግዳ ተቀባዩ በገዛ ራሱ ግርግም የተወለደውን ሕፃን ሳያየው ቀረ።

ማርያምና ዮሴፍ ሕፃኑን ይዘው በተቻላቸው ፍጥነት ወደ ግብፅ ገሠገሡ። ድንበሩን ከተሻገሩ፣ ከሄሮድስ ግዛት ውጭ ወጡ ማለት ነው። ዮሴፍ ደግሞ ሥራ ያገኛል። ነዛ ሰብአ ሰገል ያመጡላቸውን ውድ ስጦ ዎች ንደ ምንም ብለው ይዘዋል። ነዚህን ሸጠው ለምግብና መጠለያ የሚሆን በቂ ገንዘብ ያገኛሉ፣ አይደለም ንዴ?

6

«ወንድ ሕፃናት ሁሉ ይገደሉ!»

ንጉሥ ሄሮድስ በኢየሩሳሌም ከተማ ባለው ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሆኖ ትዕግሥት በማጣት ይጠባበቅ ነበር። የምሥራቆቹ ጠቢባን ንደገና ወደ ኔ ዘንድ ይመጣሉ በማለት ይጠብቃቸው ነበር።

ሰብአ ሰገል የአይሁድ ንጉሥ የሆነውን ሕፃን ፈልገው ወደ ቤተ መንግሥቱ መጥተው ነበር። በሕፃኑ ንጉሥ አሳብ ምክንያት ሄሮድስ አንዳንዴ በሚጥል በሽ ተመትቶ ነበረ። ሄሮድስ በአሁን ጊዜ ሽምግሎና ምሞ የነበረ ቢሆንም፣ ጨካኝ መሆኑን ግን አሁንም አላቆመም ነበር። በዘመኑ ሁሉ የለየለት ጨካኝ ሆኖ ኖሯል።

ጠቢባኑ ነርሱ ዘንድ ከመጡ ብዙ ቀናት አልፏቸዋል፣ አሁን ደግሞ የሚመለሱበት አንገብጋቢ ጊዜ መሆኑን ርግጠኛ ነበር። ያንዳንዱ ሰዓት ዓመት መሰለው። ከራሱ ጋርም ያወራ ነበር።

«ከመ መሜ በፊት ሰዎች ንዳያውቁኝ ሆኜ በመገበያያ ቦ በ ነርሱ መሃል መገኘት ችል ነበር። የሚሉትንም ሁሉ አዳምጥ ነበር። ማን ማኝ ንደ ሆነና ንዳልሆነ ለይቼ አውቅ ነበር። ማኝ ያልሆኑትን ለይቶ፣ አስሮ መግደሉ ቀላል ጉዳይ ነበር። ከሐዲዎች ወይም ንቢተኞችን አል ገሳቸውም። ክሕደትና ምቢተኝነት ለ ኔ ያው ነበሩ።

« ነዚያ የምሥራቅ መኳንንት የት ናቸው? ያንን መናጢ ሕፃን ሲያገኙት ተመልሰው መጥተው ንዲያሳውቁኝ ነግሬአቸው ነበር። < ኔም ንድሰግድለት> ነበረ ያልኳቸው። ሃ! ሃ! ሃ! ኔማ በአሳቤ ንድገድለው ብዬ ነበር ንጂ - ንድገድለው!

« ዲያ የት ናቸው? በቤተ ልሔም ብዙ ቆዩ ኮ። ምናልባት ያንን ዙፋን ነጣቂ ማግኘቱ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ወይኔ፣ አሁንስ አልቻልኩትም።»

ሄሮድስ ተንቀጠቀጠ፣ ቡጢ ጨበጠ፣ የበለዙትን የሸማግሌ ጥርሶቹን አፋጫቸው።

«ዔሊዔዘር! ዔሊዔዘር!» ሲል ተጣራ።

«አቤት፣ ግርማዊነትዎ፣» ሲል መለሰ።

«ዔሊዔዘር፣ ንደ ለማኝ ልበስና ወደ ጐዳናዎቹ ውጣ። በመገበያያ ስፍራ ቆመህ የሚባለውን አዳምጥ። በደንብ አዳምጥ። የሰማኸውንም መጥተህ ንገረኝ። ትሰማኛለህ? ወዲህ ተመልከት፣ ሺ?»

ዔሊዔዘር መሬት መሬቱን ከማየት ቀና ብሎ ለትንሽ ጊዜ ንጉሡን አየት አደረገ። አስቀያሚውንና አስጠሊ ውን የንጉሡን ፊት ማየት አልቻለም። ለዓመ ት በጥርጣሬ፣ በግድያና በክፋት ተ ሞልቶ ይ ይ የነበረው መልክ፣ አሁን ደግሞ በሽ የሄሮድስን ፊት ለመ የት አስፈሪ አድርጎ ል።



«በል ሂድና አዳምጥ፣ ትሰማኛለህ? በተለይ የውጭ ተጓዥ ዜጋ ዎች የሚያወሩትን ልብ ብለህ አዳምጥ። ካየሃቸው ወዲያውኑ መጥተህ ንገረኝ፣ በፊት ዚህ መጥተው የነበሩና - - - ፍለጋ የመጡቱ።»

«ግርማዊነትዎ፣ የአይሁዶቹ ሕፃን ንጉሥ።»

«ከ ኔ በቀር የአይሁድ ንጉሥ ብሎ ነገር የለም፣ ላቁ ሄሮድስ ብቻ!» አለና ሄሮድስ ንደ አንበሳ አገሳ።

«ይቅር ያድርጉልኝ፣ ግርማዊነትዎ። ስሕተት የተናገርሁት አውቄ አይደለም» አለ ዔሊዔዘር የተርበተበተ።

«የምትናገረውን አስብ፣ ያለበለዚያ ጭንቅላትህን ጣለህ! ነዚያን ጠቢባን ሰዎች የት ንዳሉ መፈለግ አለብህ። ፈልጋቸውና በቶሎ መጥተህ ንገረኝ።»

ዔሊዔዘር ለጊዜው ለማኝ መስሎ ሄደ።



ሄሮድስ ትዕግሥት አጣ፣ ቀባጠረ፣ ዓጽም በሆኑ ጆቹ ትራሱን በቡጢ ደበደበው። በመጨረሻም፣ ዔሊዔዘር ተመልሶ መጣ። «ግርማዊነትዎ፣ ወደ አገራቸው ተመልሰው ሄደዋል፣» አለ ዔሊዔዘር ያለከለከ።

«ሄደዋል? ሄደዋል?» አለ ሄሮድስ።

«አዎን። በቤተ ልሔም ብዙም አልቆዩም አሉ። አንድ ሌሊት ብቻ ነው ያደሩት። በኢየሩሳሌምም በኩል አላለፉም። ይህንን የሰማሁት ለሥራ ጉዳይ ከቤተ ልሔም መጥቶ ዚህ በኢየሩሳሌም ካለ አንድ ሰው ነው። ነዛ ጠቢባን ሰዎች ከቤተ ልሔም ሲወጡ ግመሎቹ በሕይወ ቸው ፈጥነው በማያውቁበት ሁኔ ፈጥነው ንደ ሄዱ ለአንድ ሌላ ሰው ሲያጫውት ሰምቼዋለሁ። ተጣድፈው ነበር፣» ሲል ነገረው ዔሊዔዘር።

ሄሮድስ ተናደደ። «የዘቦቹን አለቃ አምጣልኝ!» ሲል በመላ ቤተ መንግሥት ስኪሰማ ድረስ አንባረቀ።



ከዚያም፣ ንዲህ ሲል ለራሱ ተናገረ፣ «የለም፣ ላሳድዳቸው አልችልም፤ ከግዛቴ ሥር አይደሉም። ደግሞም አስማተኞች ናቸው፣ አስማተኞች፣ አስማተኞች። ኔ- ኔ- ኔ በአስማተኞች ላይ ምን ማድረግ ንደምችል አላውቅም። የለም፣ የለም፣ አንድ የተሻለ ዕቅድ ያስፈልጋል።

«አ፣ አ፣ ሻምበል፣ ወ ደሮችህን ወደ ቤተ ልሔም ሄደው ከሁለት ዓመት ዕድሜ በ ች የሆኑ ሕፃናት ወንድ ልጆችን ንዲገድሉ ዘዛቸው፣» አለ።



የዘቡ ሻምበል ለመናገር . . . . . ብሎ አፉን ሲከፍት ንጉሡ አቋርጦ፣ «የለም፣ ንዳትከራከረኝ! *ሁለንም በነፍስ ወከፍ*፣ በደንብ ሰምተኸኛል? አንድ ንኳ ቢያመልጥህ፣ በ ርሱ ምትክ አንተ ራስህ ትሞ ለህ።»

«በአካባቢ ያሉትን ወረዳዎች፣ የ ርሻ ቦ ዎችንም ሳይቀር ቃኛ ቸው! በምኩራቡ ያለው ጸሐፊ የ ያንዳንዱ ተባዕት ልጅ ስም ዝርዝር ይኖረዋል። ስማቸውን ና መኖሪያቸውንም መፈለግህ ንዲሁም ይህ *የንጉሡ* ት ዛዝ መሆኑን ንገረው። *በአስቸኳይ* ይህንን ንድ ደርግ!»

ምስኪኑ የዘቦች አለቃ ዘገነነው። አንዳንዶቹ ጓደኞቹ ሕፃን ወንድ ልጆች ነበሯቸው።

ግዚአ፣ ንዴት አሰቃቂ ነገር ነበር፣ ናቶች አለቀሱ . . .

ወንድሞችና ቶችም አለቀሱ . . . አባቶችም አለቀሱ . . . ሴት አያቶች፣ ወንድ አያቶች ሁሉ አለቀሱ። አጎቶችና አክስቶች፣ የአጎትና የወንድም ልጆች ሁሉ አለቀሱ። ወዳጆችም ሳይቀሩ አለቀሱ። ቤተ ልሔም በጎዘን ውስጥ ገባች።

ያ ኩይ ሽማግሌ ንጉሥ ግን ኢየሩሳሌም ባለው ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ሆኖ ትንሽ ደስ አለው፣ ምክንያቱም የአይሁዶችን ሕዛኑን ንጉሥ ያስወገደው መስሎት ነበርና ነው።

ይሁን ንጂ፣ ስሙ በምኩራቡ ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ አንድ ሕፃን ቀርቶ ነበር። ጸሐፊው ስሙን ይዞት ነበር፣ ሕፃኑ ግን የትም ሊገኝ አልቻለም። ጠፍቷል። የት ንዳለ ማንም አላወቀም።

አምን፣ ሕፃኑ ኢየሱስ የገባው ግብፅ አገር ነበር። ወደዛው የሄደው በ ኩለ ሌሊት ነበር። ሲሄድ ማንም አላየውም። ንደሚሄድም ማንም ያወቀ አልነበረም። ናቱ ንኪ መንገዱን ስለያዙ ድረስ መሄዳቸውን ገና አላወቀችም ነበር። አሳዳጊው አባቱም ለማንም ሰው አልተናገረም፣ ምክንያቱም ኩለ ሌሊት ግዚአብሔር በሕልም ስለ ነገረው ነበር። በዚያን ሰዓት ተነሥቶ ያየም የሰማም አልነበረም። ርሱ በአዲሱ ቤቱ በግብፅ አገር ሰላምና ጤና ነበረ። በመልካም ሁኔ ም ያድግ ነበረ።

ያ ክፉ ሽማግሌ ንጉሥ፣ ሄሮድስ ንደ ረካ ለረጅም ጊዜ አልቆየም። ከልጆቹ ቀሪ የሆነው አንቲጳተር ዙፋኑን ሊወስድበት የሞከረ መሰለውና ሄሮድስ ልጁን አንቲጳተርን አስገደለው። ንጉሡ ብዙ ወንድ ልጆች የነበሩት ቢሆንም፣ ብዙዎቹን ገድሏቸዋል። ሄሮድስ ንግዲህ ንዲህ ዓይነቱ ሰው ነበረ። ለነገሩ፣ ሄሮድስ ራሱ ለመኖር የቀሩት ወደ አራት ወይም አምስት ቀኖች ያህል ብቻ ነበር። ያንን ግን ርሱ አያውቅም ነበረ።

አንቲጳተር መሞቱ ሲነገረው ከፍተኛ የ ፎይ ስትንፋስ ተነፈሰ። በዚያ በሚያስፈራ አፉ ፈገግ አለ፣ የ ጆቹን ጣቶች ሳይሆን ጣፋጮችን አላመጠ።

ደስ ው ግን የቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነበር። ንደገና ንዴቱ ተነሣበት። ተናናቂው የሚጥል በሽ ው ተመለሰበት።

ቅዠቱ በረከተ። በሚያሳዝን ሁኔ የሚወዳት ሚስቱን ስም የጠራ «ማርያምኔ! ማርያምኔ!» ያለ አለቀሰ። ርሷንና የሚያምሩ ወንዶች ልጆ ን ካስገደላቸው ዓመ ት ተቁጥረዋል። ትዝ ዋ ግን ከዛ ጊዜ ጀምሮ ሌሊት ሌሊት ያሳደደው ይገኛል። የቤተ መንግሥቱ ሠራተኞች ብዙ ጊዜ ንጉሡን ሌሊት ሌሊት፣ «ማርያምኔ! ማርያምኔ . . . !» ያለ ሲጣራ ሰምተው ል።



አሁን የተጠላው ሽማግሌ ንጉሥ የመጨረሻውን ትንፋሹን በጣር የተነፈሰ ያለ ንደገና የማርያምኔን ስም መጥራት ጀመ ረ። ለመጨረሻ ጊዜ የሚጥል በሽ ው ተነሥቶበት መሬት ላይ ሲንከባለል ሊረዳው የተጠጋው ማንም አልነበረም። አገልጋዮቹና ጠባቂዎቹ ዝም ብለው በመቆም አሰቃቂውን አሟሟት ተመለከቱ።

ከዚያም፣ «ሄሮድስ ሞቷል!» የሚል ልፈፋ ተሰማ።

በመላው ስራኤል ላቅ የመገላገል ፎይ ንደ ሆነ ተ ሰማ።

ዜናው ወደ ሮም፣ አውግስጦስ ቄሣር ዘንድ ተላከ። ከጊዜ በኋላም አውግስጦስ ቄሣር የሄሮድስን ልጅ አርኬላዎስን በይሁዳ ምድር ገዢ አድርጎ ሾመው።

በግብፅ፣ ማርያምና ዮሴፍ ንደዚሁም ትንሹ ኢየሱስ ለጥ ብለው ተኝተው ነበር። ዮሴፍ ገና ሳይነጋ ነቃ። አልጋው ላይ ንደ ተጋደመ ጸጥ ና ደስ የተሞላ ሰላም ዙሪያውን ንደ ከበበው ተሰማው።

«አሃ፣» አለ ለራሱ። «አዎ፣ ያ ውብና ወዳጅ የሆነ መልአክ ንደገና መጥቷል። መልአክ ወደ ኔ መጥቶ ሲናገረኝ ሦስተኛ ጊዜው ነው። በ ውነቱ አሁን መልካም ዜና ነው። <ሕፃኑን ሊገድሉት ያሳድዱት የነበሩ ሞተዋል። ሞተዋል! ሄደዋል!>። አሁን ሕፃኑን ይዘን ወደ አገራችን ወደ ስራኤል መመለስ ንችላለን።»

ማርያምና ዮሴፍ በግብፅ የነበሩ ወዳጆቻቸውን ተሰናበቱ። በግብፅ የሚኖሩ ብዙ አይሁዶች ነበሩ። ከትንሹ ኢየሱስና ከትንሹ (ከውርንጭላ) አህያቸው ጋር ሆነው ጉዟቸውን ጀመሩ።

ወደ ስራኤል መንገዳቸውን አቅንተዋል። ድንበሩ ላይ ሲደርሱ አሁን ገዢው አርኬላዎስ መሆኑን ሰሙ። ርሱም አስፈሪ፣ ጨካኝ የሄሮድስ ልጅ ነበረ፤ ሽማግሌው አባቱን የሚስተካከልና ከመገደል ያመለጠ ነበረ።

ማርያምና ዮሴፍ ወደ ስራኤል የተጓዙ ያወሩ ነበር። «ምናልባት ኮ ይሄ አርኬላዎስም ደግሞ ሕፃኑ ኢየሱስን የፈለገው ይሆናል፣» አለች ማርያም።

«መልአኩ ንዳለ፣ የሕፃኑን ሕይወት የሚሹ ሞተዋል፣» አላት ዮሴፍ። «መልአኩ ያለው ይህንን ነው፣ ኛ ግዛቱንም ንተ ውለ ለን። ቤተ ልሔም፣ ኢየሩሳሌምን ትተን ወደ ሰሜን ወደ ናዝሬት ንሄዳለን፣» አላት።



በ ርግጥ፣ መንገዱ ረጅም ነበረ። በመጨረሻ ላይ ግን ወደ ናዝሬት የሚወስደውን ተራራ በመውጣት ላይ ነበሩ። ቤት መድረስ ደስ ይላል። ትንሿ ቤ ቸው ትተዋት ንደ ሄዱ፣ ንደዛው ጠበቀቻቸው - ጠረጴዛው፣ ዮሴፍ የሠራው አልጋ፣ ማሰሮው፣ ጨርቆቹ (ምንጣፎቹ)፣ ጌጣጌጦቹ - ሁሉም አቧራውን ማራገፍ ይፈልጋሉ ንጂ ዛው አሉ። ከቤቱ ጋር ተጣብቆ ደግሞ የአናጢው መሥሪያ ክፍል፣ ማለትም የዮሴፍ የሥራ ክፍል ነበ ረች። በጣም የሚኮራባት የሥራው ክፍል ነበረች። አሁንም ቢሆን ይኮራባ ል። ክምር ንጨቶቹ ልክ ንደ ተዋቸው ነበሩ። አግዳሚውና የመሣሪያ ዕቃዎቹም ዛው ነበሩ። በመሣሪያ መስቀያው ላይ ግን የጐደለ ነገር ነበር፣ ሆኖም ከ ርሱ ጋር የወሰዳቸው ስለ ነበሩ ከግብፅ የገዛቸውን ሌሎች አዲሶች መሣሪያ ዎችን ጨምሮባቸው ይዟቸው መጥቷል።

«አሁን፣ ማርያም፣» አላት ቅፍ አድርጎ ይዞ፣ «አሁን፣ በ ግዚአብሔር ጸጋ ልጁን ናሳድገዋለን። ጐበዝ አናጢ ንዲወጣው የመጋዝ አጠቃቀምና የጣውላ አላላግን አስተም

ረዋለሁ። ግዚአብሔር አናጢ ንዲሆን ፈልጎት ነው ንጂ ወደ ኛ አይልከውም ነበር፣» አለ።

« ኔ ደግሞ ፊደል አስተምረዋለሁ፣» አለች ማርያም ደግሞ በበኩሏ። «ማንበብንና መቀጠርንም አስተምረዋለሁ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሪኮችን ንዲሁም ስለ ተፈጥሮ ነግረዋለሁ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ንደ ሌሎች ልጆች በቃል መሸምደድ አለበት፣ ቃል በቃል። ምኩራብ ትምህርት ቤት ከመግባቱ በፊት አንዳንዱን ነገር ንኳን ማወቅ አለበት።»

ሐሜትና ሹክሹክ ንደ ነበረ የተረጋገጠ ነው። ወደ ናዝሬት ንደ ተመለሰች ሁለት ሴቶች ከው ጉድጓድ አጠገብ ሆነው ሲናገሩ ማርያም ሰማቻቸው።

« ንግዲህ ከዚህ ሁሉ ጊዜ በኋላ ማርያምና ዮሴፍ ተመልሰው መጡ። ለመሆኑ ሄደው የነበረው ወዴት ነበር? ሕፃኑንስ አየሽው?»

«አዎን፣ ደስ የሚል ሕፃን ነው። የማን ይሆን? ብዬ ገ ረማለሁ። ውነት ማን ንደ ሆነ ግርም ይለኛል።»

«ዮሴፍ ነው ብዬ፣» ብላ ሳትጨርስ አንዷ።

«ኡስ - ስ- ስ!- ከኋላሽ ነው ያለችው» አለቻት ሌላዋ።

ዳሩ ግን፣ ማርያም ሰዎች ለሚሉት ነገር ጉዳይዋ ነው? ይህንን ለወራት ሰም ዋለች። ርሷ ንደ ሆን ሕፃኑ ማን ንደ ሆነ ውቀዋለች፣ ዮሴፍም ንዲሁ የሕፃኑን ማንነት ያውቃል። ሌ ሎች ሰዎችን በተመለከተም ግዚአብሔር በራሱ ጊዜ፣ ሊያውቁ ለሚፈልጋቸው ሁሉ ራሱ ይነግራቸዋል።

ማርያም ንደ ሆነች የም ስበውና የም ሰላስለው ብዙ ድንቅ ነገሮች ነበሯት፣ ከዚህ በፊት ያየቻቸውና የሰማቻቸው ነገሮች ሁሉ ሕያው ሆነው በአ ምሮዋ ሲ ወሱ የሚኖሩ አሉ። ቤቷ ውስጥ ብቻዋን ስትሆንና ሕፃኑም ሲተኛላት፣ ጀ ን አጣጥፋ ቀጭ በምትልበት ጊዜ፣ አብዛኛው ጊዜ ወደ አሳቧ የሚመጡት ወደ ግርግሙ መጥተው የጠየቋት ረኞቹ ነበሩ። መሊሑን፣ ሕፃኑን

ሲያመሰግኑና ሲሰግዱለት ይሰማት ነበር። የቤተ መቅደሱ ሽማግሌው ስምዖንንም በአሳቢ ይመጣባ ል፣ አሮጊቷ ነቢይት ሐና ደግሞ ግዚአብሔር መሢሑን ንድ የው ስለ ፈቀደላት ስ መሰግነው በአሳቢ ትሰማ ለች።



ማርያም ዓይኖ ን ትክል አድር ጋ በርቀት ስትመለከት ባያት ቁጥር፣ ዮሴ ፍ፡- «ላርቆ አሳብሽ ትሸለሚያለሽ» ይላት ነበር። ማርያም ደግሞ ፈገግ ብላ፡ - «አዬ፣ ዮሴፍ፣ ነዛ ሰብአ ሰገል ከ ነ ስ ጦ ዎ ቻ ቸ ወ ፡ በ አ ፤ የ ሰ ፡ ስ ፊት ተንበርክከው ሲሰግዱ የ ዩኝ ኮ ነው። በዛ ጭር ባለው ምድረበዳ አልፈው ርሱ ወዳለበት ወደ ቤተ ልሔም የመራቸው ደማቁ ኮከብ ሲያስቡት ይገርማል፣» ትለው ነበር።

ነገር ግን፣ ግዚአብሔር፣ ኢየሱስ ማን ንደ ሆነ ለማንም ከመናገሩ በፊት ጥቂት ጊዜ ማለፍ የግድ ነበረበት። ግዚአብሔር ራሱ ካልነገረው ደግሞ በ ውነት ማንም ሊያምን አይችልም።

ሕፃኑ ኢየሱስ በማደግ ላይ ነበረ። የሚወደድ፣ ደስ የሚል ትንሽ ልጅ ነበር። ኔም ሆንኩኝ ናንተ ርሱ በሦስትና በአራት፣ በአምስትና በስድስት፣ በሰባትና በስምንት፣ በዘጠኝና በአሥር ንዲሁም በአሥራ አንድ ዓመቱ ምን ያደርግ ንደ ነበረ ለማወቅ ብንወድም አንዳች ነገር ንኳ ልናውቅ አንችልም። ይሁን ንጂ፣ ስለ አሥራ ሁለት ዓመቱ የሚናገር አንድ ሪክ ግን አለን።

7

አናጢ ለመሆን መሠልጠን

«ጠበቅ አድርገህ ያዝ፣ ኢየሱስ! ጅ ውን በ ይል ልመ ው ነው። ቦ ው ላይ ማስገባት አለብን፣» አለ ዮሴፍ።

ኢየሱስ አሥራ ሁለት ዓመቱ ነበር፣ ወደ አሥራ ሦስተኛ ዓመቱ ሊሸጋገር ነበር። ናዝሬት በሚገኘው የአናጢ መሥሪያ ቤቱ ውስጥ ሆኖ የገበሬው ስምዖንን ማረሻን ሲያበጁ ዮሴፍን የረዳው ነበር።

«አሁን ገልብጣት፣ ጐሽ! አሁንም! በቃ ያዝ አሁን! አሁን ልክ ነው።»

ትዋ! አሁንም ደግሞ ሌላ ምት።

ዮሴፍ ትንሽ ገቢ ያለው ጥሩ ሥራ ነበረው። ንደ ጠረጴዛ፣ አልጋ፣ ቡፌ፣ በር፣ ንዲሁም ማረሻ፣ ለበሬ የሚሆን ቀንበርና ሌ ሎችም ብዙ የሚሠሩ ነገሮች ተከምረዋል። አንዳንዴ ደግሞ፣ ዮሴ ፍ የቤት ሕንፃ ሥራን ለመሥራት ወጣ ይል ነበረ።

አብዛኛውን ጊዜ ልጆች ያለቀሱ ከጐዳና ወደ አናጢ መሥሪያ ቤቱ የሮጡ ይመጡ ነበር።



« ባክህን ዮሴፍ . . . ባክህን ኢየሱስ . . . አሻንጉሊቴን ጠግኑልኝ::»

« ባክህን የመጫወቻ መኪናዬን ሥራልኝ::»

አሁን የገበሬው ስምዖን ማረሻ ተራ ሆነ::

ያኔ ማርያም ከቤ ቸው ጋር ወደ ተያያዘው የአናጢ መሥሪያ ቤት መጥ በራፉ ላይ ቆመች::

«ለአንድ ደቂቃ ላነጋግርህ ፈልጋለሁ፣ ዮሴፍ፣» አለችው ማርያም:: «ምን መሰለህ፣ ሁለት ልጆች በአንድ ጉዳይ ላይ የተ ጣሉ ነው፣» አለች፣ ጫጫ ውና ውካ ው ከቤቱ ውስጥ ይሰማ ነበር::

« ባክህን፣ ኢየሱስ፣ ትንሽ ጊዜ ካለህ፣ ሄደህ ልጆቹን አረጋጋቸው! ከ ነርሱ ጋር ጥሩ ትግባባለህ:: ኔ ስከምመጣ ከ ነርሱ ጋር ቆየኝ፣ ብዙ አልቆይም፣» አለችው ናቱ ማርያም::

ስለዚህ፣ ኢየሱስ ማረሻውን ትቶ ወደ ቤቱ ሄደ:: ብዙ ሳይቆይ የደስ ሳቅ ተሰማ:: ልጆቹ ንደገና ደስ አላቸው::

ዮሴፍ ፊት ለፊቱ ማረሻውን አጋድሞት ሳለ፣ ማርያም መጣችና፣ «ዮሴፍ፣ ሳስብ ነበር፣ ና አንድ ነገር መጣልኝ:: ከጥቂት ሳምን ት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ስትሄድ ከአንተ ጋር ሄጀ በወቅቱ በሚከበረው የፋሲካ በዓል ላይ ለመገኘት ፈልጋለሁ:: ይህ ዓመት ለኢየሱስም ልዩ ዓመት ይሆንለ ል:: ርሱ ከአንተ ጋር ይሄዳል:: ኔም አብሬአችሁ መሄድ ፈልጋለሁ::»

«መልካም፣» አለ ዮሴፍ፣ «ማርያም፣ አንቺ አብረሽን ከመሆንሽ የበለጠ የሚያስደስተኝ ሌላ ምን ነገር ይኖራል? ሌሎቹን ልጆች ግን ንዴት ደርጊያቸዋለሽ? በጣም ትናንሾች ናቸው:: መጣላት የሚጀምሩት ገና ፊትሽን ስ ዞሪ ነው::»

«አዎ፣ ዮሴፍ አውቃለሁ:: ነርሱን ትቶ የመሄድ አሳብ ያስጨንቀኛል:: ቢሆንም ግን በዚህኛው ዓመት ፋሲካ ቤተ መቅደስ ብሄድ ደስ ይለኛል:: ለኢየሱስ የመጀመሪያው ነው፣ ኔንም ቢሆን

ንድገኝ የሚያነሣሣኝ ነገር አለ።»


«መልካም፣ ውዴ፣ ንዴት ንደሚቻል ደግሞ ናያለና። ምናልባት ልጆቹን የምትይዝ ሴት ናገኝ ይሆናል፣ ስክንመጣ ትጠብቃቸዋለች፣» አላት ዮሴፍ።

« ኔም ከሰው ጋር ቢቆዩ ደስ ይለኛል፣ ዮሴፍዬ። ዚህ ያሉትን መሥሪያ ዕቃዎችን አንዳንዶቹ በጣም አደገኞች ናቸው። ልጆቹ ዚህ ይገቡና በመጋዙም በመላጊያውም ሲጫወቱ ጣቶቻቸውን ሊቆርጡ ይችላሉ። ልጆች ንደማይነኩ ቃል ቢገቡም ንኳ፣ ምን ንደሚያደርጉ ውቃለህ። ቃላቸውን ይረሱና ወደ ማበላሸቱ ይገባሉ።»

«ከ ኛ ጋር መሄድሽ ግሩም አሳብ ነው፣ ማርያም። ናመቻ ቸዋለን። አንዳንድ ነገሮች ተሳክተው፣ ሰው ይገኝና አንቺም ለመሄድ መንገድ ይመቻቻል። ገና ጊዜ አለ፣» ብሎ ሲያበቃ፣ ማርያም ወደ ቤት ለመሄድ ፊቷን መለሰች።

«ማርያም፣ ይህንን ማረሻ ለመጨረስ ንዲያግዘኝ ኢየሱስን ላኪልኝ፣» አላት ዮሴፍ።

ኢየሱስ በትናንሾቹ ልጆች ጨዋ መሃል ነበረ። ርሱ ወለሉ ላይ የዳኸ ሲሄድ፣ ነርሱ ደግሞ ጀርባው ላይ ወጥተው ይጫወቱ ነበር።



«ተባረክ ልጄ፣ አንተ የልጆችን አያያዝ ውቃለህ። አሁን ግን የገበሬው ስምዖንን ማረሻን ሠርቶ ለመጨረስ ለ ርዳ በመሥሪ ያ ቤቱ ትፈለጋለህ። በዚህ ዓመት በሚከበረው የፋሲካው በዓል ላይ ለመገኘት ዐቅጃለሁ፣ ያንተም ልዩ የፋሲካ በዓል ይሆናል። መገኘት በጣም ፈልጋለሁ፣» አለች ማርያም።

ኢየሱስ የደስ ፈገግ አሳየ፣ ና ማረሻውን ለመያዝ ፈጥኖ ሄደ። ሥራውም ቶሎ አለቀ።

ማርያም ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ትችል ዘንድ ከማርያም ቶች መካከል ሰሎሜ የምትባለው አንዷ ልጆቹን ለመያዝ ፈቃደኛ ሆነች። ርሷ ንዳለችው፣ ከራሷ ልጆች ጋር ቤት መቆየታ የማይቀር ነገር ነበር። ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ በቤተሰቡ መሀል የነበረው መልካም መግባባት ተቋርጦ ነበር። ቤተሰቡ ጉዳዩን ማወቅ ተስኖአቸው ነበር። ያ ግን አሁን አሥራ ሁለት ዓመት ሆኖ ል፤ ነገር ግን፣ አንዳንዱ አንድ ነገር ከሆነ በኋላ፣ የሆነው ሆኗል ብሎ መተው በቤተሰብ መካከል ያለ ነገር ነው። በተ ጨማሪም፣ ሁሉም ኢየሱስን ይወዱት ነበር። የአክስቱ ልጆች የሆኑት ሕፃናት ርሱ በጣም ጥሩ ነው ብለው ያስቡ ነበር።

«ሁልጊዜ ጨዋ ን በዳኝነት ንዲመራልን ንጠይቀዋለን። ርሱ ሁልጊዜ ሚዛናዊና ቸርም ነበር። በሚያደርገው ነገር ሁሉ ራሱን መጨረሻ ያደርጋል፣» ይሉ ነበር።

ስለዚህ፣ አክስት ሰሎሜ አደገኛ የአናጢ መሣሪያዎች በሌ ሉበትና መሥሪያ ቤት ባልሆነው በገዛ ራሷ ቤት ውስጥ ልጆቹን ወስዳ ለመጠበቅ ቃል ገባች።

«አሁን ሁላችሁም አክስት ሰሎሜን ከብሯ ላችሁ፣ ጥሩ ልጆች ትሆናላችሁ፣ አይደል?» አለቻቸው ና ቸው።

«አዎ፣ አዎ። አንቺ ደግሞ ከቤተ መቅደሱ ብራና ይዘሽልን ትመጫለሽ አይደል?» አሏት። ይህ ትንሽ ብራና የፍጥረት ሪክ፣ ጥቂት የምስጋና መዝሙር፣ ንዲሁም ከሕግ ጥቂት ክፍሎችን የያዘ ስለ ነበር፣ ልጆች ይወዱ ል። ከቤተ መቅደሱ ተገዝቶ የሚመጣ ትንሽ ብራና ካለህ ጥሩ የጊዜ ማሳለፊያ ነበር።



« ና ትንሽ የኢየሩሳሌም ከረሜላ። ና ትንሽ . . . ና ትንሽ . . .» ያሉ ይቀጥሉ ነበር።

« ሺ፣ ሺ፣ ውድ ልጆቼ፣ ዓቅሜ ቢፈቀደልኝ መጠን ገዛላችኋለሁ። ስመለስ፣ አክስት ሰሎሜ ጥሩ ልጆች ንደ ነበራችሁ ከነገረችኝ፣ የማደርግላችሁን ኔ አውቃለሁ፣» አለቻ ቸው።

«ማርያም!» አለና ዮሴፍ ተጣራ። «ተዘጋጅተሻል፣ የ ኔ ቆንጆ? በግማሽ ሰዓት ውስጥ መዘጋጀት አለብን። ሌሎቹም ሰዎች የሚንቀሳቀሱበት በዚሁ ጊዜ ነው። ከናዝሬት የምንሄደው ብዙ ሰ ዎች ነን። አሁን መሥሪያ ቦ ዬን ስለ ዘጋጋሁ፣ ምን ጊዜም ልንንቀሳቀስ ንችላለን፣» አለ ዮሴፍ።

«መልካም፣ ዮሴፍ፣ ኔ ንደሆን ዝግጁ ነኝ፣ ነገር ግን ልጆቹ

የዳቦ ፍርፋሪ ጥለው ንዳይሆን ቤቱን የፈ ተሸኩ ነበር። ቤቱን ንደ ሆነ በደንብ አጽድቼዋለሁ። ሥራዬን በደንብ አጠናቅቄያለሁ፣ ርሾውን ደፋፍቻለሁ፣ ምንም ፍርፋሪ አልቀረኝም። በፋሲካ ጊዜ በቤት ውስጥ ትንሽ ፍርፋሪ ወድቃ መገኘት የለባትም። ለመጨረሻ ደጋግሜ ፈትሼዋለሁ። ስለዚህ፣ አዎ፣ ተዘጋጅቻለሁኝ። ኢየሱስ?» አለች ማርያም።

« ንዴ፣ ልጆቹ ኮ አሁን ርሱን ፍለጋ መጥተው ነበር። ወንዶቹ ቀድመውን አልፈዋል፣ ነገር ግን ግንቡን አልፈው ንዳይሄዱ ነግሬቸዋለሁ፣ ስከምንደርስባቸው ዛው ንዲጠብቁን ነግሬያቸዋለሁ። ሕፃናት ንዳልሆኑ አውቃለሁ፣ ሁሉም አሥራ ሁለት፣ አሥራ ሦስት፣ ከዛም በላይ ናቸው። ቢሆንም ልንጠብቃቸው ያስፈልጋል።

«በአህያው ላይ ምግብና የመኝ ምንጣፍ ተጭነዋል። አየሩ ድንኳን ተክሎ ለማደር ምቹ ነበር። ንደዛው ንደሚቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ። ደስ የምንለኝበት ይመስለኛል፣ ማርያም። ንዴ፣ ለፋሲካ የሚሆነውን የቤቱን ቀይ የወይን ጠጅ በአቁማዳ ሞልቼ አህያው ላይ ጭኜዋለሁ ለካ። ሁሉን ይዘናል መሰለኝ፣ ይኸውና መጡ!» አለ ዮሴፍ።

ወዲያውኑ ዱብ ዱብ ንዲሁም ኪኪኪ የሚል የብዙ ሰዎችና የአህዮች ኮቴ ድምፅ ተሰማ። በ ርግጥም፣ ከናዝሬት ወደ ኢየሩሳሌ ም የሚደረገው ያ ረጅም ጉዞ ተጀምሯል።



ዮሴፍ ከሌሎቹ ሰዎች አህያዎች ጋር አብሮ ይሄዱ ዘንድ ትንሹን አህያቸውን መንገድ አስያዘው። ማርያም ደግሞ የትንሿን ቤ ቸው ቀ·ልፍ አስቀመጠችና ከሴቶቹ ጋር ተደባለቀች።

ናቶች ስለ ተዉዋቸው ልጆች በመስጋት ይነጋገሩ ነበር።

ወዲያውኑ ግን፣ ከተጨነቁት መካከል ንዲህ የሚል አሳብ ፈለቀ፡- «ግን ኮ ብዙ አንቆይም። ሳምንቱን ሙሉ ዛ መቆየት የለብንም። ምናልባት ሁለት ወይም ሦስት ቀን ብንቆይ ነው። ለመሄድ ብቻ አምስት ቀን ንደሚወስድ የ ወቀ ነው፣ ሲመለሱም ንደዚሁ። አይ፣ ተዉት፣ ተዉት!» ተባባሉ።

ሴቶቹ ንደ ትናንሽ ልጆች ግድ የሌላቸው ሆኑ!

ወንዶቹ ጉዞ ላይ ሆነው ስለ ብዙ ነገሮች አወጉ። ስለ መከር . . . ስለ ቀረጥ፣ አይ፣ የቀረጡ ነገር! መምህሩ ሒለል ስለዚህ ምን ይል ይሆን? . . . በዚህ ጉዳይ ላይ የመምህሩ ስምዖንስ አስተ ያየት? «መሢሕ» የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ ሲነገር ይሰማል። የሚመጣው መቼ ይሆን?

ዮሴፍ ንደሆነ መሢሑን ሊገልጠው የሚችል ግዚአብሔር ብቻ ንደ ሆነ ያውቃል፣ ስለዚህ አስተያየቱን አልሰጠም።



ወንዶች ልጆቹ ወደ ፊት ሮጡ፣ ወንዶቹ ንደሚያደርጉት፣ ወንዞችን ማግኘት፣ የወፎችን ጐጆ ማደን፣ ጥንቸሎችን ማባረር ነው ሥራቸው- ከዚያ ደግሞ ቡድኑ ላይ ለመድረስ መሽቀዳደም።

ወቅቱ የፀደይ ወር ነበር። የመንገዱ ዳር በዱር አበቦች ተሞልቷ ል- ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ ነጭ አበቦች ይ ያሉ። ሐምራዊና የወይን ጠጅ ቀለም ያላቸው አበቦች በዛፎች ላይ ፈክተ ውና ተንጠልጥለው ይ ዩ ነበር። ከነፋሻው አየር ጋር ሽ ቸው ያውዳል። የወፎች ዝማሬ ደግሞ አንዳንዱ ውይይቱንና ሳቁን አልፎ ይሰማ ነበር።

መንገደኞቹ በጉዟቸው ላይ ያሉ ለቁርስ ለውዝ፣ ቴምር፣ በለስና የበቆሎ ድርቆሽ ይበሉ ነበር። ሲመሽ ደግሞ ድንኳን ተ ክለው ይሰፍራሉ። ሳት አቀጣጥለው ራ ቸውን አብስለው በልተ ው ይተኛሉ። በማግሥቱ ንደገና ጉዟቸውን ይቀጥላሉ።

ና በዚህ ሁኔ ተጓዙ።



«ነገ ማ ዛው ንደርሳለን፣» አለች ማርያም፣ ርሷና ዮሴፍ ደግሞም ኢየሱስ ከሌሎቹ ተጓዦች ጋር ሆነው በመጨረሻ በሰፈሩበት ስፍራ ራ ቸውን የበሉ ሳለ።

«አዎን፣» አለ ዮሴፍ፣ «ከዛ በፊት ግን ኢየሩሳሌምን ናያ ለን። ጠመዝማዛውን መንገድ ካለፍን በኋላ ኢየሩሳሌም ብቅ ትላለች- በፀሐይ ብርሃን አማካይነት ወርቃማ ሆና ስ ብለጨልጭ ት ያለች። ወርቃማ የወይን ዘለላዎቹንም በቤተ መቅደሱ ግንብ ላይ ተንጠልጥለው በፀሐይ ብርሃን ሲያብለጨልጩ ዩዋቸዋላችሁ፣» አላቸው ዮሴፍ።

«ወይ ጉድ፣ ዮሴፍ፣ ዛሬ ማ ስ ባለ ቅኔ ሆነሃል!» አለች ማርያም።

«ኢየሩሌምን አስመልክቶ ልገልጠው የማልችለው አንድ ነገር አለ። የብር ጡሩምባዎች ሲነፉ ከሩቅ ትሰማላችሁ፣ ገና ዛ ከመድ ረሳችን በፊት የመሥዋዕቶቹ ሽ ይሽት ችኋል።»

«ይህንን መንገድ ከዚህ በፊት ሄጀበ ለሁ ኮ፣ ዮሴፍ!» አለች ማርያም። «የሕዝብ ቁጠራውን ስ ውሰው የለ?» አለችው ቀጥላ።

«ከቶ መቼ ይረሳኛል ብለሽ ነው!»

ከ ራት በኋላ ተጓዦቹ በ ሳት ዙሪያ ሆነው ያወጉ ነበር። ተ ጓዦቹን ይመሩት የነበሩት የምኩራብ ር ሰ መምህር ጮክ በማለት ንዲህ አሉ፡- «ልጆች፣ ስለ ፋሲካ ደስ የሚላችሁን ነገር ስቲ ንገሩን፤ ምን ደስ ይላችኋል? ማስ ወስ ስከ ቻላችሁበት ጊዜ ድ ረስ በቤ ችሁ ሆናችሁ ፋሲካን ስ ከብሩት ኖራችኋል። ፋሲካ የትም ይከበር የት፣ ያው ፋሲካ ነው፤ አሁን የምናከብረው በኢየሩሳሌም ስለሚሆን ለአንዳንዶቻችሁ ለየት ሳይልባችሁ አይቀርም። ስቲ ከፋሲካ አከባበር ውስጥ ከሁሉ የበለጠ ደስ የሚላችሁ ነገር ምንድን ነው?»

«የበግ ጥብስ ከመራራው ቅጠል ጋር ደስ ይለኛል፣» አለ አንዱ።

«ያ ጥሩው ቀይ የቤት የወይን ጠጅ ደስ ይለኛል፣» አለ ሌላው።

« ኔ ደስ የሚለኝ ከትምህርት ቤት ማረፋችን ነው፣» አለ ሦስተኛው ተናጋሪ።



« ኔ ትኩስ ዳቦ ወዳለሁ፣ ስለዚህ ማዬ ማ ማ የሻገተ ውን ንጀራ ሁሉ ስትጥለው ደስ ይለኛል። አንድ ቀን ንኳ ያልዋለ ትኩስ ዳቦ ናገኛለን፣» አለ አራተኛው።

«ለፋሲካ ተብሎ የሚደረገው የፀደይ ጽዳት ደስ ይለኛል። በዚህ ጊዜ ምንም የሚገኝ ቆሻሻ ነገር የለም። ማዬ ሁሉንም ነገር ጥሩ አድርጋ ጸዳዋለች።»

« ንዴ፣ አንተ ትንሽ አ ፍርም ንዴ? ባንተ ዕድሜ ነገሮቹን ሁሉ በንጽሕና መያዝ አለብህ ኮ!» አለ ከልጆቹ መካከል አንዱ።

«መልካም ልጆች፣ ያላችሁት ነገር ሁሉ ደስ የሚል ነው። በ ርግጥ አስተሳሰባችሁ ትንሽ ቁም ነገር የጎደለው ነው፣ ያው ልጆች ምን ጊዜም ልጆች ናቸው፣» አሉ መምህሩ።

«ለዚህ ምሽት ይበቃል ከማለ ችን በፊት፣ በኢየሩሳሌም ለምናከብረው በዓል ሊያዘጋጀን የሚችል ትክክለኛውን የፋሲካ ሪ ክ ከ ናንተ መሀል ሊነግረን የሚችል ካለ ይንገረን። አንተ ለምን አትጀምርልንም ዮና ን? አሥ።»

ሳቱ የተንቀለቀለና የተንጣጣ ንዲሁም ፍንጣሪው ወደ ሌ ሊቱ ሰማይ የተወነጨፈ ያለ፣ ልጆቹ ከመጀመሪያው የፋሲካ ሪክ ተነሥተው ሙሴ የ ግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑትን ስራኤ ላውያንን ከግብፅ ባርነት ንዱት መርቶ ንዳወጣቸውና ንዱት መንግሥት ለመመሥረት ንደ በቁ ያወሱና ጣልቃ የገቡ በዚያ ላቅ ሪክ ላይ የተቻላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ጀመሩ። ልጆቹ የራሳቸው የሆነ የአተራረክ ዘይቤ ነበራቸው። ከዚያ ከናዝሬት ተነሥቶ በ ሳት ዙሪያ ተቀምጦ ከነበረው ቡድን የሚወጣው የደስ ሳቅ አሁንም አሁንም ንደ ድምፀ-መረዋ ያንቃጨለ አካባቢውን ሞላው።

« ግዚአብሔር ይስጥልኝ፣ ልጆች፣» አሉ መምህሩ። «አሁን ደግሞ ከ ናንተ መካከል ሊያጠቃልልን የሚችል ማን ነው?»

« ኔ፣» አለ ዮና ን። «ፋሲካ የምስጋና ጊዜአችን ነው ማለት ችላለሁ፣ የዛሬ ስንት ዓመት ሙሴ ሕዝባችንን ከጠላቶቻቸው፣ ከግብፃውያን ነፃ ስላወጣቸው ግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ጊዜ ነው። መሢሐችን ሲመጣ ደግሞ ኛን ጠላቶቻችን ከሆኑት ከሮማውያን ነፃ ያወጣናል።»

«ኡስ! ኡስ!. . .»

«ስለዚህ፣ ልጆቹ በፋሲካ ጊዜ ግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ብዙ ነገር አለ ማለት ነው። የሐሴት ጊዜ ነው። ማስ ወስ ከቻ ላችሁበት ጊዜ ጀምሮ በየቤ ችሁ ሆናችሁ ያከበራችሁት ነው። ይህ በኢየሩሳሌም የሚከበረው ግን ለ ናንተ የተለየ ነው። ይህ ፍጹም ልትረሱት የማትችሉት ትልቅ ገጠመኝ ነው።

«አሁን ደ ና ደሩ! ነገ በኢየሩሳሌም ንገናኛለን!»

8

የአባቱ ሥራ

ተጓዥ ቡድን ወደ ኢየሩሳሌም የቀረበ የቀረበ በሄደ ቍጥር፣ መንገዱ በሰው ብዛት አይ ይም ነበር። ጨለማ ለበሰ። አይሁዳውያን ተጓዦች ሳይቀሩ ከተለያዩ ከተሞችና መንደሮች ተነሥተው ሁሉም ወደ ምሥራቅ በማምራት ፋሲካውን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ገሠገሡ።

በዓሉ ከመከበሩ አንድ ቀን ቀደም ብላችሁ በሄሊኮፕተር የበ ረራችሁ የኢየሩሳሌምን ዙሪያ ብ ዩት ኖሮ፣ መንገዶቹ በሰውና በአህዮቻቸው ብዛት ተጨናንቀው ዩዋቸው ነበር። ነዚህ ሁሉ ወደ ከተማው ማዕከል ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ለመግባት የሚገሠግሡ ናቸው። መንገዶቹ ከአንድ ግዙፍ ሸክርክሪት ወጥተው ወደ አንድ ትልቅ መሰኪያ የሚሰኩ ዘንጦች ይመስሉ ነበር። ትልቁ መሰኪያ ኢየሩሳሌም ነበረች።

በጐዳናዎቹ ማለፍ ብትችሉ፣ በከተማዋ ምድር ቤት ሥር ባሉት



የቤቶች መስኮት ውስጥ፣ «የሚከራይ፣» «ሙሉ የመኝ አገልግሎት፣» «መኝ ና ቁርስ፣ ከፋሲካ ራት ጋር . . . » «የበግ ጠቦት ይቀርባል፣» «የራሳችሁን ወይን ጠጅ ይዛችሁ ኑ፣» የሚሉ ማስ ወቂያዎችን ማየት ትችሉ ነበር።

ማንኛውም የቤት ባለቤት ያንዳንዷን ስንዝር ክፍት ቦ ንግዳ ለመቀበያ ተጠቅሞባ ል። በሺህና በሺህ የሚቈጠሩ ተ ጓጮች የፋሲካ በዓሉን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተዋል። ስለዚህ አንዳንዶቹ ውጭ ማደር ግድ ሆኖባቸዋል።

በበዓሉ ስለ መገኘት ርግጠኞች የሆኑ ንግዶች ዓምና ይዘውት የነበረውን መኝ ንዲያዝላቸው ቀደም ብለው መመዝገባቸው ጥርጥር የለውም።

መስተንግዶው በጣም ቀላል ነበር። የሚያስፈልገው ጋደም የሚሉበት ቦ ብቻ ማግኘት ነው። ከመሥዋዕቶቹና ከፋሲካው ዝግጅት የሚገኝ ምግብ ሞልቷል።

በ ነዚህ የአይሁድ መንገደኞች የሮም ወ ደሮች ሁልጊዜ የቅርብ ክትትል ቢያደርጉባቸውም፣ ከጥንት ጓደኞች ጋር መገናኘ ቱና ባህላዊውን የፋሲካ ደስ አብሮ መካፈል ደስ ይል ነበር። አንዳንድ ረብሻም ሊኖር ስለሚችል ጥበቃ ይደረጋል!

ማርያም፣ ዮሴፍና ኢየሱስ የሚያርፉበት ስፍራ አገኙ። ንጹሕ አየርን የተነፈሱ ለብዙ ኪሎ ሜትሮች ከተጓዙ በኋላ፣ በዚያ ሌ ሊት የ ንቅልፍ ኪኒን ያስፈለገው ማንም አልነበረም። በልብስ ማስጨያ ሽቦ ላይ ቢንጠለጠሉ ንኳ በመልካም ንቅልፍ ተ ወስደው የሚ ደርበት ሁኔ ነበር!

ማለዳ ላይ የመጀመሪያው የወጋገን ጮራ ንደ የ፣ በቤተ መቅደሱ ጫፍ ላይ ሆኖ ሲጠባበቅ የነበረው ካህን በብርማው ጥሩምባው ሦስት ጊዜ ነፋ።

በዚህ ጊዜ ኢየሩሳሌም ከ ንቅልፏ ነቃች። በቤተ መቅደሱ የነበሩ ካህናት ልዩ ወደ ሆኑት ተግባሮቻቸው ሄዱ። ለዕለቱ ሥራ ድልደላ በካህናቱ መሃል ዕጣ መጣል ነበረበት። በ ርግጥ አንዳንድ ሥራ

ዎች አሰልቺ ነበሩ። ይሁን ንጂ፣ አሰልቺ ሥራም ቢሆን፣ ዕጣ የደረሰው ካለ ያለ ምንም ማጉረምረም፣ አድልዎ ተፈጽሞብኛል ሳይል መቀበል ነበረበት።

ሽማግሌው ዘካርያስ፣ የኤልሳቤጥ ባለቤት፣ ምርጥ የሆነ ሥራ፣ ያም በቅድስቱ ውስጥ ዕጣንን ማጠን በዕጣ ንደ ደረሰው ስ ውሳለህ? አንተም ካህን ብትሆን ኖሮ በዕጣ ምን ዓይነት ሥራ ንደሚደርስህ ማወቅ ፍጹም አትችልም ነበር። የሚያስገርም ነበር።

ካህናቱ የሚኖሩት ሥራቸውን ቀጥ አድርገው ይዘው ነበር። በቤተ መቅደሱ ውስጥ ብዙ የሚሠሩ ሥራዎች ነበሩ።


ማርያም፣ ዮሴፍና ኢየሱስ ከ ንቅልፋቸው የነቁት፣ ልክ ንደ አስተናጋጆቻቸውና በቤቱ ንደ ነበሩት ንግዶች ሁሉ፣ በዛው በብራማው ጡሩምባ ድምፅ ተቀሰቅሰው ነበር። (በነፍስ ወከፍ ቤቱ የተቻለውን ያህል ንግዳ ይዞ ንደ ነበር አትርሳ።)

ቁርስ በጣም ቀላል ነበረ። ኩፍ ያላለ ቂጣ፣ ምናልባት ደግሞ ጥቂት የዓሣ ቋንጣ፣ ትንሽ የወይራ ፍሬና ፍራፍሬዎች ነበሩ። ከዚያም ሁሉም ተነሥተው ወደ ቤተ መቅደሱ ሄዱ።

የጧት ፀሐይ ጮራ ኰረብ ው ላይ በነበረችው ቤተ መቅደስ፣ በነጭ ምነበረድ በተገነባው የቤተ መቅደሱ ግንብ ላይ ሲያንጸባርቅ፣ ያየ መቼም ቢሆን ት ይንቱ ከአ ምሮ አይጠፋም።

ርግቦች ኩኩሉ ሲሉ፣ ድንቢጦች ጪርብ፣ ጠቦቶች ደግሞ በ - - · ሲሉ ይሰሙ ነበር። ሰጋጆቹ የ ላቁን ቤተ መቅደስ ደረጃዎች የወጡ ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰደውን የጥንት መዝሙር ይዘምሩ ነበር። ትላልቆቹ በሮች ብርግድ ብለው ተከፍተዋል። ሰጋጆቹ ቀደም ብለው በቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ተ ሰብስበዋል። ዚህ ላይ ማርያምና ዮሴፍ መለያየት ስለ ነበ ረባቸው፣ ማርያም ሴቶች በሚሆኑት በኩል ስትሆን፣ ዮሴፍ ደግሞ ኢየሱስን ይዞ በወንዶች በኩል ሆነ። ቤቱ ያሳረፋቸውም ሰውዬ የገዛውን በግ ይዞ አብሯቸው ወደ ቤተ መቅደሱ ሄዶ ነበር።

ለኢየሱስ ንዴት ያለ ግሩምና የተለየ ቀን ነበር። የ ርሱ ኩዮች የሆኑ ሌሎች ወንድ ልጆች ከአባቶቻቸው ጋር መጥተው ነበር። የመጀመሪያውን የፋሲካ ራት መስሎ ነበረ።



ካህናት ለመሥዋዕት የመጡትን በጎች ለመሥዋዕት የተገቡ መሆናቸውን ለመመርመር በዚያው አካባቢ ነበሩ። ለመሥዋዕት የሚቀርቡት ፍጹምና ንከን የሌላቸው ሆነው መገኘት ነበረባቸው። ስለ ያንዳንዱ ቤተሰብ አንድ በግ ለ ግዚአብሔር መሠዋት ነበ ረበት። ስቡና ኩላሊቱ ንደሚቃጠል መሥዋዕት ሆነው መቃጠል ነበረባቸው። በመጀመሪያው ፋሲካ፣ በግብፅ በነበረው የ ስራኤ ላውያን ቤት ላይ ንደ ተረጨ ሁሉ፣ አሁንም የበጉ ደም ስለ ቤተ

ሰቡ ጢአት ሲባል በ ላቁ መሠዊያ ፊት መረጨት ነበረበት።

ረፋዱ ላይ የቤተሰቡ ላፊ የሆነ ሰው ለመጠበስ ዝግጁ የሆነውን የበግ ሥጋ ለማምጣት ሄደ። ወደ ቤቱ ወሰደውና ለራት ይቀርብ ዘንድ ተጠበሰ፣ በዚህ ጊዜ ቤተሰቡና ንግዶቹ (ንደ ማርያም፣ ዮሴፍና ኢየሱስ የመሳሰሉት) ተገኝተው የተጠበሰውን የበግ ሥጋ ከነማባያዎቹ፣ ማለት ከመራራ ቅጠላ ቅጠል (ንደ ኛ አዋዜና ሰናፍጭ መሆኑ ነው)፣ በቂጣ ያጣቀሱ በመመገብ፣ በበዓሉ ራት ይደሰቱ ጀመር። ቂጣው ርሾ ስላልተደረገበት አልነፋም ነበር። ይህ ያልነፋ ቂጣ ነዛ የተቻኮሉት ስራኤላውያን ከግብፅ ሲወጡ የጋገሩትን ቂጣ ይመስል ነበር። በዚያ ሌሊት ዳቦውን ኩፍ ለማድረግ ጊዜ አልነበረም!

ፋሲካው የክብር በዓል ቢሆንም፣ ላቅ ትርጉምም ነበረው። ቤተሰብ፣ ዘመድ አዝማድና ንግዶቹ ሁሉ ለመመገብ ተሰበሰቡ። በነፍስ ወከፍ ንግዳ አራት አራት ጽዋ ሙሉ ቤት የተጠመቀ ቀይ ወይን ጠጅ ይዞ መጣ።

የመጀመሪያው ጽዋ የወይን ጠጅ ተቀዳ። ቡራኬ ተደረገበት። ከዚያም ሁሉም ጠጡ። ቀጥሎ ደግሞ ሁሉም በጐድጓዳ ሳሕን



ጆቻቸውን የነከሩ ጠቡ። (ከመብላት በፊት ጅን መ ጠብ በጣም አስፈላጊ ነገር ነበረ።) ሌላ ጸሎት ተደረገና የሁለተኛው ጽዋ ወይን ጠጅ ተቀዳ።

ከዚህ በኋላ የቤቱ የመጀመሪያው ልጅ፣ «ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው?» ብሎ ጠየቀ። ትልቅ ሰው ትርጉሙን አብራራ። ከዚያም ግዚአብሔር አያት ቅድመ - አያቶቻቸውን ከግብፅ ባርነት ስለ ማውጣቱ የሚናገረውን የምሥጋና መዝሙር ሁሉም ዘመሩ።

ከዚህ ቀጥሎ የሦስተኛውን ጽዋ ወይን ጠጅ ጠጡ። ከዚያም ሌላ ጸሎትና ምስጋና ተደርጎ አራተኛው ጽዋ የወይን ጠጅ ደግሞ ተቀዳ - ጽዋዎቹ በጣም ትላልቅ አልነበሩም። ከዚህም በኋላ የምስጋናን መዝሙር ዘመሩ። ሁሉም በጣም ደስተኞች ነበሩ።

በመጨረሻም የተጠበሰው የበግ ሥጋ ተቆራረጠና ከነሙሉ ዝግጅቱ ተስተናገደ።

ከፋሲካው ምሽት በኋላ ወንዶቹ ልጆች አልተከለከሉም። ንደገና ወደ ቤተ መቅደሱ ንዲሄዱ ተለቀቁ። ዛ ብዙ ነገር ይደረግ ነበር። ከነበሩት መምህራን ጋር ወዳጅነትን አበጁ። የጥናት ጊዜ ተዘጋጀላቸው። አሁን ጎላፊነት የሚወስዱ ዜጎችና የ ስራኤል ሰዎች ንዲሆኑ የሚያበቃቸው ዕድሜ ላይ ደርሰው ነበር። የሚተኙበት ቦ ከበቂ ምግብ ጋር ዛው ተዘጋጅቶላቸው ነበር። በየቀኑ ብዙ መሥዋዕት ይቀርብ ስለ ነበር፣ በቂ ምግብ መገኘቱ የሚደንቅ አይደለም። ልጆቹ በሥራ ለመርዳት ፍላጎት ንዳደረባቸው መገመት አትችሉምን?

አሁን ማርያምና ዮሴፍ ሥራ የበዛባቸው ምስኪን ሰዎች ነበሩ። ዮሴፍ የዕለት ምግቡን ለማግኘት በርትቶ መሥራት ነበረበት፣ ማርያም ደግሞ ቤተሰቡን ማስተዳደር ነበረባት። ስለዚህ ንደ ጨ ረሱ ፈጥነው ወደ ቤ ቸው ለመመለስ ዐቀዱ። ሕጉ የሚደነግገው ከፋሲካ በዓል ሁለት ቀን በኋላ ሰዎች ለትናንሾቹ መሥዋዕትና ቡራኬ ሥርዓት ብለው መቆየ ቸው በጣም አስፈላጊ ንዳልነበ ረ ነው። ስለዚህም ሕዝቡ ወደየቤቱ መመለስ ይችል ነበር።



«ኢየሱስ ነገ መሄዳችንን ያውቃልን?» ሲል ዮሴፍ በሁለተኛው ሌሊት ጠየቃት።

« ንዴ፣ በደንብ ንጂ። ማወቅ አለበት፣» ስትል መለሰች ማርያም።

«ግሩም፣ ነገ ጧት ወደ አገራችን ለመሄድ ንነሣለን፣» አለ ዮሴ ፍ።

በ ርግጥም ደግሞ ንዳለው ተነሡ። ብዙ ሰዎች በዚያን ማለዳ ኢየሩሳሌምን ጥለው ወጡ። መንገዶቹ በሕዝብና በአህያዎቻቸው ብዛት ተጨናንቀው ነበር። ዮሴፍ፣ ዮና ንና ስምዖንን አያቸው። አዎን፣ ልጆቹ ከቤተ መቅደሱ ሳይመጡ አልቀሩም።

በመጀመሪያ፣ ጉዞው ግፊያ የሞላበት ነበር። ከፊት ለፊት ያለውን ሰው ግር ሳይጠልፉ ማለፍ የማይቻል ነገር ነበር። በኋላ ግን፣ የመረማመጃው ስፍራ ሻል ያለ መሄዱ በጀ።

ወንዶችና ሴቶች ለየብቻቸው በቡድን ሆነው ቀኑን ሙሉ ሲጓዙ ዋሉ። ወንዶች ልጆቹ ግን በየቦ ው ነበሩ። አንድ ቦ ብዙም አይ ዩም። አንዳንዱ ወሬ ለመስማት ተናጋሪዎቹን ከብበው ይ ዩ ነበር፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ሌላ ስፍራ የጋለቡ ይሄዱ ነበር።

የመጀመሪያው ቀን ንደዚህ አለፈ። ከናዝሬት የመጣው ቡድንና ሌሎቹ በሰፈሩበት ቦ ነበሩ። ሳት ተቀጣጠለ፣ ምግብም በ ሳቱ ዙሪያ ቀረበ። ቤተሰቦች በአንድ ላይ ተሰባሰቡ። ርስ በርስም ይፈላለጉ ጀመር።

ማርያምና ዮሴፍም ነበሩ።

« ንዱ፣ ኢየሱስ የት አለ፣ ዮሴፍ?» አለች ማርያም።

« ኔ ንጃ። ካንቺ ጋር አልነበረም ንዱ? ቀኑን ሙሉ አላየሁትም፣» አለ ዮሴፍ።

«የለም፣ ከ ኔ ጋር አልነበረም። ካንተ ጋር የነበረ መስሎኝ ነበር። ኔም ሙሉ ቀን አላየሁትም። ልጆቹስ ቢሆኑ የት ናቸው?» አለች ማርያም።

«ሁሉም ዚህ ናቸው መሰለኝ፣» አለ ዮሴፍ።

ዮሴፍ አንዳንድ ልጆችን ጠየቀ።

«ኢየሱስን?» ሲሉ ጠየቁ። «ከ ኛ ጋር አልነበረም። ቀኑን ሙሉ አላየነውም። ከመነሣ ችን በፊት፣ ጧት አይቼው ነበር፣ ከአንድ መምህር ጋር ይነጋገር ነበረ። ከወንዶቹ ቡድን ወይም ከሴቶቹ ቡድን ጋር ያለ መስሎኝ ነበር። ኋላ ከማን ጋር ነበር ይባላል?» አለ ከ ነርሱ መሃል አንዱ።

«አንተ ንደምትመጣ አውቆ ነበር፣ ስምዖን?»

« ኔ ንጃ። አላነጋገርሁትም። ከአንዳንድ መምህራን ጋር ሲነጋገር ነበር። በ ርግጥ ይመጣል ብዬ አስቤ ነበር።»





«ምናልባት መነሣ ችንን አላወቀ ይሆናል። ወይኔ፣ ዮሴፍ!» ብላ ማርያም አለቀሰች።

« ንግዲህ፣ ማርያም አትጨነቂ! ርሱ ራሱን መጠበቅ የሚችል ትልቅ ልጅ ነው፤ ከቀሩት ጋር ይመጣል፣» አላት ዮሴፍ።

ዳሩ ግን፣ ናቶች ንዴት ንደ ሆኑ ውቃላችሁ። ማርያም ተሸበረች። ንደ ፈነ ወይም አንድ ነገር ንደ ሆነ ርግጠኛ ሆነች።

ማርያም አስጨናቂ ሌሊት አሳለፈች። ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሳ ከመሄድ በቀር ጭንቀቷን የሚያስ ግሥላት ሌላ ነገር አልነበረም።

« ሺ፣» አለ ዮሴፍ። «ተመልሰን ሄደን ንፈልገዋለን። ምናልባት ወደ አገሩ ሲመጣ መንገድ ላይ ናገኘው ይሆናል፣» አላት በመቀጠል።

ተስፋ ሰጭ አነጋገር ቢሆንም፣ ብቻውን መጓዙ አደገኛ ነበረ። መንገድ ላይ ለስግደት የሄዱትን በርከት ብለው በቡድን ሲመለሱ አገኙአቸው። ብዙ ሕዝብ ወደ አገሩ በመመለስ ላይ ነበር።

«ልጄን አላያችሁም?» ስትል ማርያም ጠየቀቻቸው። «አሥራ ሁለት ዓመቱ ነው፤ ጠፍቶብናል» በማለት ማርያም ለማስረዳት ሞከረች። ስትጨነቅ ጊዜ ያምማት ነበር።

ማንም አላየውም።

ኢየሱስ ከዚያ ቡድን ጋር ንደ ነበረ ማርያም በጣም ርግጠኛ ነበረች። አሁን ልጁን ንድትጠብቀው የተሰጣትን የ ግዚአብሔርን አደራ ችላ ያለችው መስሎ ተሰማት። ዮሴፍም በበኩሉ የሕሊና ወቀሳ ቢሰማውም፣ ሊያጽናናት ሞከረ። ኢየሱስ ከሕዝቡ ጋር የተ ጓዘ ነው ብለው መገመት ብቻ አልነበረባቸውም።





ማርያምና ዮሴፍ ተመልሰው በኢየሩሳሌም በሰነበቱበት ቤት ሲደርሱ ፀሐይ ጠልቃ ነበር። የለም፣ ዚያም አልነበረም። ሌላ የጭንቀት ሌሊት። ማርያም መብላትም ሆነ መተኛት አልቻለችም።

ጧት ተነሥተው፣ ገበያ ስፍራና ልጅ የሚገኝበት ሌላ ስፍራ ፈልገው ካጡት በኋላ፣ የመጨረሻ ተስፋቸው ወደ ቤተ መቅደሱ መውጣት ሆነ።

በ ርግጥም ዛው አገኙት! ያገኙት ሲናገራቸውና ጥያቄዎችን ሲጠይቃቸው በአድናቆት ያደምጡት ከነበሩት የሃይማኖት መምህራን ጋር ተቀምጦ ነበር። በኢየሱስ አስተዋይነትና ጥልቅ በሆኑ ጥያቄዎቹ ተገርመው ነበር። የሕግ አዋቂ አስተማሪዎቹ፣ ከአይሁድ ልጆች ውስጥ ንደ ርሱ ያለ ከቶ አጋጥሞአቸው አያውቅም።

ማርያም ምንም ል ደርግ አልቻለችም። ምንም አልቻለችም። ርሷ ለሦስት ቀን ያህል በጭንቀትና በውጥረት ንደ ነበረች የውስጧን ንዲህ ስትል ተነፈሰች፦ «ለምን ንዲህ አደረግኸን? አባትህና ኔ በጣም ስንፈልግህ ነበር። በሁሉ ስፍራ ፈለግንህ፣» አለችው።

«ስለ ምን ፈለጋችሁኝ?» አለ ኢየሱስ። «በአባቴ ቤት መገኘት ንደሚገባኝ አላወቃችሁምን?»

ማርያምና ዮሴፍ ግን ምን ማለቱ ንደ ሆነ ሊረዱት አልቻ ሉም። ኢየሱስ መምህራኑን ደ ና ሁኑ አላቸው፣ ፈገግ አለና ሻንጣውን ለማምጣት ሮጠ። ቶሎ ብሎ ከማርያምና ዮሴፍ ጋር ወደ ናዝሬት ለመመለስ ተዘጋጀ። ኢየሱስ ወደ ናዝሬት ተመልሶ ማርያምና ዮሴፍን ይ ዘዝ ንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግ ረናል። አሳቡን ሁሉ በቤተ መቅደሱ ያደርገው ከነበረው ውይይት ሁሉ መልሶ ቤቱ ያከናውነው ወደ ነበረው ንደ ማረሻ ጥገና ሥራና ትናንሽ ልጆችን ወደ ማጫወቱ ተመለሰ።

«ኢየሱስ፣ ኔ ዜዳለሁ፣ ምድጃው ላይ ያለውን ዓሣና በመጋገሪያው ውስጥ ያለውን ዳቦ ያየህ፣ ጐሽ» ብላው ማርያም ንስራዋን ተሸክማ ው ልትቀዳ ወደ ው ው ጉድጓድ ሄደች።

«ኢየሱስ!» ዮሴፍ ነበር የተጣራው። «ይህንን አግዳሚ ጣውላ ንድትይዝልኝ ፈልጌህ ነበር።»

ማርያም ይህንን ሁሉ በልብዋ ትይዘው ነበር።

ኢየሱስም በ ግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወደደ ሆኖ፣ በጥበብና በቁመት አደገ።

ስ ውሳላችሁን?

ምዕራፍ 1. ኣንድ ደማቅ ኣዲስ ኮከብ

1. ኮከብ ቁጣሪዎቹ ለኢየሱስ ይዘውለት የሄዱት ስጦ ዎች ምን ነበሩ?
2. ኢየሱስን ናገኘዋለን ብለው ያሰቡት የት ነበር?
3. ሽማግሌው የኣይሁድ ንጉሥ ስሙ ማን ይባል ነበር?

ምዕራፍ 2. ንጉሥ ሄሮድስ ተቈጣ

1. መሢሑ ይወለዳል ተብሎ የሚ ሰበው የት ነበር?
2. መሢሑ የት ንደሚወለድ ለንጉሥ ሄሮድስ የነገረው ማን ነበር?
3. ሄሮድስ ለሰብአ ሰገሉ ያደርጉ ዘንድ ያዘዛቸው ምንድን ነበር?

ምዕራፍ 3. «ስሙም ኢየሱስ ይባላል»

1. ማርያምና ዮሴፍ ለሕፃኑ የሚወጣው ስም ማን ንደ ሆነ ያወቁት ንዴት ነበር?
2. መልኣኩ መሢሑ ያደርጋል ያለው ምን ነበር?
3. ዮሴፍ ናዝሬት ወዳለው ቤ ቸው ቶሎ መመለስ ንዳለባቸው ያሰበው ለምን ነበር?

ምዕራፍ 4. «ኑና መሢሑን ዩት!»

1. ወላጆቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ የወሰዱት ኢየሱስ የስንት ዓመት ልጅ ሆኖ ነበር?
2. ስምዖን ከመሞቱ በፊት ለማየት ይጠብቅ የነበረው ማንን ነበር?
3. መሢሑን ያወቀችው ነቢይት ስሚ ማን ነበር?

ምዕራፍ 5. «ኣይተነዋል!»

1. መሢሑ የነበረበትን ቤት ጠቢባኑ ያወቁት ንዴት ነበር?

2. ከዚያ በኋላ ወደ ሄሮድስ ተመልሰው ያልሄዱት ለምን ነበር?
3. ዮሴፍና ማርያም ኢየሱስን ይዘው የሸሹት ወዴት ነበር?

ምዕራፍ 6. «ወንድ ሕፃናት ሁሉ ይገደሉ!»

1. ሄሮድስ የዘቡን አለቃ ያደርግ ዘንድ ያዘዘው ምንድን ነበር?
2. ዮሴፍና ማርያም ግብፅን ለቅቀው ለመውጣት ጥሩ የነበረው ጊዜ መቼ ነበር?
3. ቀጥለውስ የት ኖሩ?

ምዕራፍ 7. አናጢ ለመሆን መሠልጠን

1. ይህ የፋሲካ በዓል ለኢየሱስ ልዩ የነበረው በምን ምክንያት ነበር?
2. በመጀመሪያው ፋሲካ የተፈጠረው ምንድን ነበር?

ምዕራፍ 8. የአባቱ ሥራ

1. ዮሴፍና ማርያም ከኢየሩሳሌም ወደ አገራቸው ሲመለሱ ሳለ የተጨነቁት ለምን ነበር?
2. ኢየሱስን ያገኙት የት ነበር?
3. ኢየሱስ ምን ሲያደርግ አገኙት?

በጸሐፊዋ የተዘጋጁ ሌሎች ተከ ይ መጻሕፍት፡-

1. አዳምና ሔዋን
2. ኖ
3. አብርሃም - ፈር ቀዳጁ
4. አብርሃም - የ ግዚአብሔር ወዳጅ
5. ይስሐቅ
6. ሕፃኑ ኢየሱስ
7. ኢየሱስ በልጅነቱ